የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ
(ወዛደሩ፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁሩ)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

ቁጥር 69 ግንቦት 20/1971

እንደገና ለኢትዮጵያ ተራማጆች የአንድነት ጥሪ

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ባለፉት አምስት ዓመታት ያካሄዷቸውን ትግሎች ታሪክ ወደፊት በሚመረመርበት ወቅት በአጠቃላይ ሁለት ታላላቅ ምዕራፎች ይኖራሉ:: የመጀመሪያው ምዕራፍ ከየካቲት 1966 እስከ የካቲት 1969 ዓ.ም. ያለው የትግል ዘመን ነው:: ይህ የሶስት ዓመት የትግል ዘመን ምንም እንኳን ብዙ መውደቅ መነሳት፣ ማጥቃትና መከላከል የተፈራረቁበት ዘመን ቢሆን ቅሉ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች በቀንደኛ ጠላቶቻቸው ላይ የአጥቂነት ቦታን ይዘው ፍጹም ሕዝባዊትና ፍጹም ዲሞክራሲያዊት ወደሆነችው ኢትዮጵያ የሚገሰግሱበት ወቅት ነበር:: ሁለተኛው የታሪክ ምዕራፍ ደግሞ ከየካቲት 1969 ዓ.ም. አንስቶ እና አሁንም የምንገኝበት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ትግል ቀስበቀስ ከአጥቂነት ደረጃ እየተፈናቀለ አብዮታችን አሁን የሚገኝበት የዝቅጠት ደረጃ ላይ የደረሰበት አስከፊ ወቅት ሆኖ እናገኘዋለን::

የመጀመሪያውን የታሪክ ምዕራፍ በሚመለከተው በኩል የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ጭቁኖች በግንባር ቀደምነት እያንቀሳቀሱ የተቀዳጁትን ድሎች እዚህ ላይ አንመለስባቸውም:: ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና መላው ዓለም ያውቃቸዋል:: በሁለተኛው ምዕራፍም ቢሆን አድሃሪ ኃይሎች በተለይ ንዑስ ከበርቴው ደርግ ከተራማጆች ለመነጠል የመነሳቱ ስራ ከተካሄደ በኋላ ደርግ ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ተንሸራቶ የወደቀበትን አሳፋሪ አዘቅት፤ ይህንን መንሸራተት አሸፋፍኖ በሉ ኢትዮጵያዊያን ላይ ያደረሰውን አሰቃቂ ግፍ ዛሬ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና መላው ዓለምም ያውቀዋል:: ስለመንሸራተቱ ጉዳይ አንባቢ በሚያዚያ ወር 1968 ዓ.ም. የታወጀውን "የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም" አንቀጽ በአንቀጽ እያመለከተ ዛሬ ከሚያየውና ከሚሰማው ጋር ያነፃጽር እንላለን:: በተራማጅ ኃይሎች ላይ ስለወረደው አወጽ ባለፉት ቁጥሮቻችን እንዳሳየነው ዛሬ በኢትዮጵያ 20 ሺህ ተራማጅ፣ ዲሞክራትና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን "ከአብዮታዊው ደርግ" እሥር ቤቶች በመማቀቅ ላይ እንዳሉ፤ ይህ ቁጥር በኢትዮጵያችን ታሪክ ምንግዜም በሆነ ተደርሶበት የማያውቅ በመሆኑ፤ ይህንን ያህል አብዮታዊያን በእሥር ቤት ሲማቅቁ በአፍሪካ ምንም ዓይነት ተወዳዳሪ የሌለው ሁኔታ መሆኑንና በዓለም ምናልባት ቺሊና አርጀንቲና እንጂ ሌላ ተወዳዳሪ ሊኖር እንደማይችል... ባለፈው ቁጥራችን ያረብነውን ገምጋሚ አንባቢ ወለብ በሉ እንደሚመለከት እንገነዘባለን::

ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ከየካቲት 1969 ዓ.ም. ወዲህ በተጠነሰሰው አዲስ የቀኝ ኃይሎች ህብረት ምክኒያት አብዮታችን ከተከላካይነትም ደረጃ ወርዶ በጣረሞት ላይ የሚገኝበት ሁኔታ አለ:: እዚህ ሁኔታ ላይ እንዴት ደረስን? የሚለውን ጥያቄ ዛሬ በዚህ፣ ጽሑፍ ለመተንተን አንችልም:: የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ምንድን ነው፤ ከዚህስ ሁኔታ ለመውጣት የኢትዮጵያ ተራማጆች ምን ማድረግ አለባቸው፤ የሚለውን ጥያቄ ለማንሳትና በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ያሉም ሆነ ያልተደራጁ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፣ ለዲሞክራቶችና ለአገር ወዳጆች ሁሉ መሰረት ሊሆኑ ይችላሉ የምንላቸውን ነጥቦች ለውይይት ለማቅረብ ነው::

የዛሬው ሁኔታ ምንድን ነው? የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ከተጠነሰሰበት ወዲህ አንስቶ ዕጣው ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ዕጣ ተለይቶ አያውቅም:: ስለሆነም አዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በኢትዮጵያ ገበሬዎች፣ ወዛደሮች፣ ወላደባብሮች፣ ዲሞክራቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አገር ወዳድ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች ላይ ሲዘምት የዚህን የፀረ ሕዝብ ጥቃት እጅግ አበር ተቀብሏል:: ስፍር ቁጥር የሌላቸው አባላት ተረሽነዋል:: በእስር ቤቶች ደጋፊዎች ታሥረዋል:: ተሰደዋል:: ተንገላተዋል:: ነገር ግን ይህ በድርጅት ላይ የተረጨው ከፍተኛ ፀረ ሕዝብ እወጃ፣ ለዚህ ፀረ ሕዝብ አወጃ ጥቂት አድርባዮች ያበዱት ተባባሪነት ጭምር ያለ ትግሉና ወይም በገዐስ ከበርቴ እለሀ ላይ የተረጨዘ ህይወት የተማገደበት፤ የብዙት ኢትዮጵያዊያን ደም የተገበረበት፤ የብዙት ጭፍጨፋ የኦሮ ተበሎ የተገመለመለበት፤ የአናት አገራችን ክበር ተበሎ የተጫለበት የአብዮት ጉዳይ ከማንኛውም በሚትና ገለሰበኝነት በራቀ ጥሞና

መታየትና መተንተን ያለበት ጉዳይ ነው ብሎ ያምናል:: መሰረት ዛሬ እንደገና ለተራማጆች ጥሪ ሲያደርግ የሚነሳበት መነሻ ይህ ነው::

ከዚህ ተነስቶ ዛሬ የኢትዮጵያን ሁኔታ ተረድቶ የወደፊቱን የትግል ጉዳና ለመቀየስ ለሚፈልግ ታጋይ ሁሉ እጅግ ገልጽ የሆኑ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮች አሉ:: ዛሬ የአገራችን እንላለን:: ይህ ያለው የፖለቲካ ጥራት ለአብዮትና ለእናት አገር ብለው ለተነሱ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ለትግል ያመች ሁኔታ ይፈጥራል:: ታዲያ ወደፊት ለምን እንራመድም? ዱሰን የቀኝ ኃይሎች ህብረት በአብዮቱ ላይ ባደረሰው ጥቃት የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ጉዳይ ከዚህ ተትሎ ይነሳል:: መልሱም አጭር ነው:: መሣሪያ የነበሩት ድርጅቶች ፈራርሰውበታል፣ ግንባር ቀደም የነበሩ እንቅስቃሴዎች በፀረ ሕዝብ አመጽና በአድርባዮች ሴራ ተኮላሽተውበታል፣ አንዳንዶቹም ተበትነውበታል:: ወደፊት ሊተቀን ይፍጨረጨራሉ:: ወደፊት ለመራመድ የግንባር ቀደም ድርጅቶች ጥንካሬ ሲያስፈልግ ፀረ ሕዝቦች እነሱን ለማፈራረስ ሲያስፈልግ ፀረ ሕዝቦች ተራማጆችን ለመለያየት ብቻ ሳይሆን በእነሱ ተጠቅመው ሌሎውን ለመ ምታት ይጃጃሉ:: ይህ ፀረ ሕዝብ ሴራቸው ደግሞ ለነሱ ጥሩ ውጤት አስገኝቶላቸዋል:: በዚህ የተነሳ ዛሬ በሃገሪቱ ላለው የፖለቲካ ጥራትና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጭቁኖች ለሚያካሂዱት የትግል ስሜትና ፍላጎት ተመጣጣኝ የሆነ የተራማጅ ድርጅቶች ጥንካሬና ህብረት የለም:: ከዚህ ተነስቶ በዛሬው ሁኔታ እንጻር የተራማጆች ትግል መያዝ ያለበት አቅጣጫ ምን እንደ ሆነ ለመገንዘብ በዚያ አያዳግትም::

ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች አንገብጋቢ ተግባሮች አንደኛ ይህ የተገኘው የፖለቲካ ጥራት እንዳይደፈርስ እቅማቸው በሚፈቅደላቸው አጋጣሚ ሁሉ መታገል፤ ሁለተኛ ለአብዮት፤ ለእናት አገር ሊንቀሳቀስ የሚችለውን ይህ ነው የማይባል ኃይል በግንባር ቀደምነት ለማንቀሳቀስ የሚያስችላቸውን የህቡዕ መዋቅር መዘርጋት፤ ሶስተኛ ደግሞ ተራማጅ ኃይሎች በሙሉ ከማንኛውም የንዑስ ከበርቴ እለሀና ወቅላነት ተፀብቀው አንድነታቸውን ማጠናከርና በህብረት መታገል አለባቸው እንላለን::

የዚህ ቁጥራችን ዋና ይዘት እንግዲህ ከሁለት ይከፈላል:: በመጀመሪያው ክፍል የጊዜውን ሁኔታ ዋና ዋና መልኮች ለማሳየት እንሞክራለን:: በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከዚህ ሁኔታ የሚፈልቁትን ተግባሮች በተለይ ደግሞ የተራማጅ ኃይሎችን ህብረት በሚመለከት በኩል አንዳንድ ሃሳቦችን ለኢትዮጵያ ተራማጆች እንሰነዝራለን::

ክፍል 1. የጊዜው ሁኔታ መልኮች

ከላይ እንዳልነው ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር የፖለቲካ ጥራት ችግር የለም:: ይህን ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህ ማለት በታሪካችን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታገልለትን ዓላማ እጅግ ጥራት ባለው ሁኔታ ያውቀዋል:: ወደዚህ ዓላማ የሚያደርሰውንም የትግል ፋና እንደዚሁ ለጠርቶ ያውቀዋል:: ከብዙ ዘመናት ትግል በኋላ ይፋ የወጣው የኢትዮጵያ ተራማጆች የትግል መድረክ ማለትም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም፣ በስተዛሬ ለሁለት ዓመታት ያህል የተካሄዱ ከፍተኛ ቅስቀሳ፣ ከሥራ ላይ እንዳዋሉ በርካ ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያዊያት ያደረሱት ደም የዚህ የፖለቲካ ጥራት መሠረት ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ፕሮግራም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋር አስከባር የተንቀሳቀሰበት መላው የኢትዮጵያ መደበኛና ሕዝባዊ ሠራዊት ያጸደቀው የገባለት ፕሮግራም ነው:: ይህ ፕሮግራም በዚህ መልክ ባገኘው ተቀባይነት የተነሳ እስከሁን ድረስ በይፋ ሽረዋለሁ ያለ ኃይል የለም:: ከመታወጁ በፊት ተያውመውት የነበረ የደርግ አባላት እንኳን ከዚያ በኋላ በይፋ አልተቃወሙትም:: እነሲሳይ ሀብቴ ሆኑ እነዓለማየሁ ፕሮግራሙን ሽረው አብዮቱን ለመቀልበስ ቢነሱም ይህንን እቅዳቸውን በሆነ ባልሆነ ተለካሽ ተወሬ ለመሸፋፈን ቀጠሩ እንጂ "ከዛሬ ወዲያ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ተሽሯል" በለው ለመናገር አልደፈሩም:: ገና ሊሆን አለ:: በሕዝቡ ፊት ባገኘው ተቀባይነት የተነሳ በይፋ ሊሽሩት የማይችሉት ቀልበሽቶችና ተንሸራታቾች ይህ ፕሮግራም በለው ጥራት የተነሳ ፊቱቸውን ባያጋልጡ በተዘዋዋሪም ቢሆን ሊሽሩት አይችሉም:: በፕሮግራሙ ጥራት የተነሳ በድርጊት ፕሮግራሙን እየተቃወሙ በአፍ በፕሮግራሙ መድረክ ላይ ነን ለማለት ፈጽሞ አዳጋች ጉዳይ ነው:: ሩቅ ሳይሄዱ መጋለጥና በሰፊው ሕዝብ መተፋትን ያስከትላል:: ፕሮግራሙ "ዲሞክራሲ ባስቸኳይ" እያለ "ታገለሀ ዉስጥ" ማለት፤ ፕሮግራሙ "ፊውዳል እንቶኔ" እያለ የመጀመሪያ ደረጃ የቢሮክራቶች አከራካሪነትን በተግባር ተመክሮ በመርገጥ፤ ፕሮግራሙ "ቢሮክራሲ ይውደም" እያለ ከዚህ ከመነሻ ቢሮክራሲ ጋር ገጥሞ የአብዮትን በፊር ማጥቃት፤ ፕሮግራሙ "በብሄራዊ ነፃነትና የግለሰብ የውጭ ፖለቲካ" እያለ የአገሪቱን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የወታደር ተቋሞች እንደገና ለአዲስ ጌቶች አስረክቦ የእናት አገራችንን ክብር እንዳልነበረ ማውደም፤ ፕሮግራሙ "ሕዝባዊ ድርጅቶች ያብቡ" እያለ ያሉትን ማጠውለግና በፀረ ሕዝብ ሴራ ማፈራረስ፤ ፕሮግራሙ "የወዛአደር ፓርቲ፣ ሌሎችም ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች" እያለ የወዛአደሩን ፓርቲ ተጋበዦች ማፈራረስ፤ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ተራማጆች እንዳይደራጁ አፍኖ መያዝ... እነዚህ ድርጊቶችና እነዚህ ሁሉ ዛሬ የቀኝ ኃይሎች ህብረት ሙሉ በሙሉ ከፕሮግራሙ መንሸራተቱን የሚያሳዩ የሚያጋልጡ

ናቸው:: በዚህም የተነሳ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን ያውቃል፤ ግን የሕዝቡን ፍላጎት እንደሚያረካ ያውቃል፤ ግን ከሕዝቡ ጎን እንደተሰለፈ ያውቃል::

ይኸንን ጥሬት ደግሞ በሰፊና በአደናጋሪ ፕሮፓጋንዳ ማደፍረስ ዘበት ነው:: ለምን? ምክንያቱም አንደኛ የዛሬ ተገሸራታቾች ራሳቸው ዛሬ የከዱትን ያሳቸውን በየአደባባዩ፤ በየስብሰባው በያለበት ገራ አሻቸው ከተከሸቸው ተነቅሉ እስኪሄዱ ድረስ ከሕዝቡ ጋር ያስተጋቧቸው የነበረ ስለነበረ ዛሬ ቃል ማጠፋቸው የአቋሞቻቸውን አዘቅት ያሳያል እንጂ ሌላ የሚያሳየው ነገር የለም:: ሁለተኛ ደግሞ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰፊና በድርጊት መሃከል፤ በሃቀኛ ወገንና በአስመሳይ መሃከል ለመለየት የሚያስችለው በቂ የፖለቲካ ንቃት ከአምስት ዓመት የአብዮታዊ ትግሉ ገብይቷል:: ከሁሉ ይበልጥ የሚሞሁና የሚደነፉ በገዩ ከሁሉ ይበልጥ የሕዝብ ወገኖች የሚመስሉበት ዘመን አከተሟል:: "የተራማጁ ተራማጁ" መስሉ የተደባለቀውን ሃሊሕአፓ ፀረ ሕዝብ ወገን ከመሃሉ እየፈለፈለ ያወጣውና ወደተራ ነፍሰገዳይነት እንዲያሽቆለቁል ያደረገው በዚህ በንቃት ነው:: የቀደሙውን የዓለማየሁ ኃይሌን የቀኝ ኃይሎች ህብረት ተለጣፊ የፖለቲካ መሥመር ፊት ለፊት ገጥሞ አሸፈረገ ያለው በዚህ በንቃቱ ነው:: ዛሬ ደግሞ ያው የነዓለማየሁ የፖለቲካ መሥመር በአዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረት አማካኝነት ሲከሰት አሸፈረገ ብሎ "ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት" ብሎ ከፀረ ሕዝቦች ጋር እጅግ አስቸጋሪ የሆነ የትንንቅ ወቀት ውስጥ የገባው ከትግሉ ከዕለት ዕለት እየተማረ፤ እስወሳጓን ከሃቀኛውን ለፈፋውን ከደርጊት፤ ለመለየት የሚያስችለው የፖለቲካ ጥሬት በማግኘቱ ነው::

ፀረ ሕዝቦችም ይኸን በታጋይ ኢትዮጵያዊያን ደም የተገኘ ጥሬት በአፈጻጸም ፕሮፓጋንዳ ለማደፍረስ፤ እነሱ ከሃዲዎች ታጋዮች፤ ታጋይ የሕዝብ ልጆችን ከሃዲዎች አድርገው ለማቅረብ ያደረጉት ጥረት በሕዝቡ ከፍተኛ የትግል ልምድና የንቃት ደረጃ የተነሳ ሙሉ በሙሉ መክሸፉን አሳጡትም:: ደርግንም ቢሆን የቸገረው ዱዩት ከንፋስ ይጠጋል ነው እንጂ ፀረ ሕዝብ እኛ ይዘን ዲሞክራሲ አያስፈልገህም፤ የእናት አገርህ ብሄራዊ ክብር ገደል ይገባ፤ የጠነባው ቢሮክራሲ ይፈንዳህ... እያሉ ወደነቃው ሕዝብ ለመጠጋትና ለዚህ ፖለቲካ የሱን ድጋፍ ለማግኘት መሞከር እንዴት ሰፋ ያለው ድንቁርና እስከምን ወደር የሌለው የሕዝብ ንቀት እንደሆነ ፀረ ሕዝቦች የተገነዘቡ አይመስሉም:: የሆነ ሆኖ ያለውን ጥሬት በሰፊው ማደፍረስ አልተቻለም:: በለሆነም ፀረ ሕዝቦች ልክ እንደኢሕአፓው ዘመን፤ ልክ እንደቀደሙው የቀኝ ኃይሎች ህብረት ዘመን፤ በአብዮቱ ኃይሎች ላይ ተሰማሩ:: ይህ በኢትዮጵያ ተራማጆች ሰፈር የተያዘው ፀረ ሕዝብ አመጽ በትግሉ ላይ ያስከተለውን ጉዳት ዝቀ ብለን እንመጠነታለን:: እዚህ ላይ ግን ለማለት የምንፈልገው አንዲት ነገር ብቻ ነው:: ይህ አመጽ ምንም ጥፋን ቢሆን፤ ምንም አስከፊ ቢሆን በአብዮቱ ሰፈር ያለውን የፖለቲካ ጥሬት አስከዚህም አላደፈረሰው:: እንዲሁም የቀኝ ኃይሎች ህብረትም ይባሱን አጋለጠው፤ ይባሱን ፀረ ሕዝብነቱን፤ ይባሱን መከበረን አባየበት እንጂ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን አላስገኘለትም:: በዚህም ሁሉ የተነሳ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሌላ ከፍተኛ የሆነ ድል ተቀዳጅቷል:: የኢትዮጵያን አብዮትና የብሄራዊ ክብሯን የወደፊት እድል ከደርግ ለይቶ፤ ከደርግ ባሻገር መመልከት ጀምሯል:: ከመጀመሪያው አንስቶ የመላ ኢትዮጵያ በሸለሰት ንቀናቄ ወደሕዝባዊት ኢትዮጵያ የሚደረገው ትግል ገዐሰ ከበርቴውን ደርግ አንድ ፋተውስቶ ደረጃ ላይ ቆሎ የሚያልፍ ትግል ነው ቢሉ ያስተጋባው የነበረው እኛ ዛሬ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አዕምሮ ውስጥ የታነፀ ሃቅ ሆኗል::

ይህ ዛሬ በሃገራችን የሚታየው የፖለቲካ ጥሬት እንዲገኝ የመላ ኢትዮጵያ በሸለሰት ንቀናቄ እጅግ የሚከራበት፤ ስፍር ቁጥር በሌላቸው አባላቱ ደም የከፈለው እስተዋጽኦ አድርጓል:: በዚሁ ሃቅ ላይ ትንሽ መለስ ብለን እንፈልጋለን::

እንደሚታወቀው የከተት አብዮት ከፈነዳ ከአንድ ዓመት በኋላ በገዘው በነበረት ተራማጁ ይባሉ በነበረት ኃይሎች መካከል ሁለት መሥመር ትግል ሲደመር ተራማጁን ወገን በመወከል መኢሶን በግንባር ቀደምነት ቢሰለፍ የቀለበሸን መሥመር በመወከል ደግሞ የኋላው ገፍስ ገዳይ ቡድን ኢሕአፓ ነበር:: በዚህ ትግል የአድሃሪያች ግንባር ቀደም የነበረው ኢሕአፓ ድል ከተመታ በኋላ የፖለቲካ ክበረታን ለመሸፈን ቢል በነፍስ ገዳይነት ተሰማርቶ እጅግ ብዙ የመኢሶን አባላትንና ደጋፊዎችን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሌሎች አብዮታዊያንን እያደነ ገደለ:: የመሥመር ትግል ኢሕአፓ ቢተፋ አልቆመም:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቀደመው የነዓለማየሁ ኃይሌ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በአንድ በኩል፤ በገዘው የነበረት የደርግ ተራማጆች መኢሶንና ሌሎች ተራማጁ ድርጅቶች በሌላ በኩል መሃከል እንደገና ሌላ ትግል ተጀመረ:: በዚህም ትግል በግንባር ቀደምነት የተሰለፈው ንቅናቄያችን አሁንም እንደቀደመው ውድ ጓዶቹን እየሰዋ በሃቀኛው መሥመር ስር መታገሉን ቀጠለ:: የነዓለማየሁ ኃይሌ የቀኝ ኃይሎች ህብረት አናት ላይ ተመቶ ከተፍረከረከ በኋላ አብዮቱ ትንሽ ባምንታት ወደፊት መገስገስ እንደጀመረ የነዓለማየሁ ኃይሌን ቀለበሸ የፖለቲካ መሥመር ይዞ ሌላ አዲስ የቀኝ ኃይሎች ህብረት ተነሳ:: የአንዳንድ የቀድሞ ተራማጆችና የአድርባይ ድርጅቶች ሠፈር መለወጥና በቀደመው በነዓለማየሁ ፖለቲካ ሥር መሰለፍ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ውዥንብርን ሊፈጥርና እስካሁን የተገኘውን የፖለቲካ ጥሬት ሊያደፈርስ የሚችል ሁኔታ ፈጠረ:: እርግጥ [illegible] አድርባይ ይህንን መገሸራቱን ለመገንዘብ የሚያስችለው ንቃት ነበረው:: ነገር ግን በዚህ ወቀት እዲሱን ዙር የመሥመር ትግል በሕዝብ በኩል፤ በአብዮት በኩል ፍንቶ ለመምራት የሚችል ግንባር

ቀደም ኃይል እጅግ አስፈላጊ ነበር:: በለሆነም መኢሶን ይህንን የግንባር ቀደምነት ኃላፊነት ያለአንዳች ማመንታት ተቀበሉ፤ ከተገሸራታቾች ጋር መገሸራትን አሻፈረገ ብሉ በአብዮቱ ሰፈር በመጽናት እንዲዓለማየሁ ከተመቱ በኋላ በተከተሉት ወራት ከፍተኛ የሁለት መሥመር ትግል ተካሄደባቸዋል:: በዚህ ትግል ውስጥ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዓር እስከዓር የነዓለማየሁን ቀለበሸ ፖለቲካ በተቃወመበት ወኔና ቆራጥነት የአዲሱን የቀኝ ኃይሎች ሕብረት መሥመር ተቃወመ:: ሚያዝያ 23 ቀን 1969 ዓ.ም. የወዝአደር ቀንን ምክንያት በማድረግ ባካየው ሰልፍ ይህ የሰፊው ሕዝብ አቋም፤ ይህ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመኢሶን ግንባር ቀደምነት ለተወረለው አብዮታዊ መሥመር ለመቀደቅ ዝግጁ መሆን ለወዳጅም ለጠላትም ይፋ ሆኖ ታየ:: በዚህም የተነሳ በሰፊው ሕዝብ ሰፈር ያለውን የፖለቲካ ጥሬት ለመቃም እዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረ፡ የኪሣራው ምልክት በሆነው ፀረ ሕዝብ አመጽ ተሠማራ::

እንግዲህ ከዚህ ወቀት አንስቶ ለመኢሶንና ለጠቀሳላው የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ያለው ምርጫ ግልጽ ነበር:: ወይ አሁንም ደርግ የያዘው መሥመር ትክክል ነው፤ አድርባይ ድርጅቶች የሚያስተጋቡት ፖለቲካ አብዮታዊ ነው፤ ብሉ በመቀላመድ ከተገሸራታቾች ጋር "አብሮ መብላት"፤ ከፀረ ሕዝቦች ጋር ተባብሮ በአብዮቱ ጣረጪት ላይ ከሚደረገው "የስልጣን ቢልዮስ" ድርሻውን ተቀብሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ መከዳት፤ በታጋይ ጓዶች ንፁህ ደም ተገኝቶ የነበረውን የፖለቲካ ጥሬት ገደል መክተት፤ ወይ ደግሞ የተያዘውን ለአብዮታችንም ሆነ ለብሄራዊ ነፃነታችን እጅግ አደገኛ የሆነውን የፖለቲካ መሥመር መታገሉንና ማጋለጡን ቀጥሉ ለማገናወኛ መስዋዕትነት ራስን ማዘጋጀት:: መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ከማድረጉ በፊት የነበሩት ሁለት ሰስት ወራት ለኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ዓይኑን አፍጥጦ ቀርቦ የነበረው ምርጫ ይኸ ነበር:: መኢሶን በታሪክ ፊት የተቀበለውን አደራ በማክበር የወሰደው ምርጫ ሁለተኛውን ጎትገ፤ የክብርና የመስዋዕትነት ጎዳና ነበር:: በነሐሴ ወር 1969 ዓ.ም. ይኸንኑ ትግል በተሻለ ሁኔታ ለመቀጠል የትግል ስልት ለውጥ ያደረገውም ከዚህ ታሪካዊ ምርጫ ተነስቶ ነበር::

ይህ እርምጃ ለመኢሶን ብቻ ባይሆን ለጠቀሳላው ለኢትዮጵያ ተራማጆች ታላቅ የፖለቲካ ድል ነው:: ይኸንን የምንለበት በዙ ምክንያቶች አሉን:: መኢሶን በዚያን ጊዜ ለቀረበለት ሁለት ምርጫ ፊት በፀረ አብዮትና በአብዮት ጎዳና መሃከል እያመነታ ቢቀጥል ኖሮ፤ "የደርግ ታሪካዊ ሚና እያበቃ ሲሄድ አብዮታዊያን ከሱ ጋር የሚያደርጉት ትብብር ያከትማል" ብሉ የገባውን ቃል ባያከብር ኖሮ፤ በደርግና በአድርባዮቹ በአንድ በኩል በመኢሶንና በሌሎች አብዮታዊያን በሌላ በኩል ያለን ልዩነቶች እንደዚሁ ግልጥልጥ ባለ ሁኔታ ተፈረጥርጦው ባይወጡ ኖሮ፤ በጥሩ የአብዮቱን ሰፈር መረከሮችና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰማዕታት የተከፈሉትን ዓላማዎች አንስቶ መኢሶን ከቀኝ ኃይሎች ህብረት ራሱን ነጥሎ ወደፊት ለመጓዝ አስፈላጊውን እርምጃ ባይወስድ ኖሮ ዛሬ አብዮታችን ይገኝበት የነበረውን የፖለቲካ ማዳገበር ማን ሊገምተው ይችላል? መኢሶን እዲሱን የቀኝ ኃይሎች ህብረት በሰፊው ሕዝብ ፊት፤ በሰፊው ሕዝብ ጋር ሆኖ መቃወሙን ትቶ እንደተቀረት አድርባይ ድርጅቶች መሪዎች በፖለቲካ መሥመር ጥያቄ ላይ ሳይሆን በቦታ ሽሚያ፤ በይገባኛል አይገባህም ውስጥ ውስጡን ቢራኮት በመታ ኖሮ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ምን ያህል አሳፋሪ የሆነ የትግል ምዕራፍ በተጻፈ ነበር? በዚህ ሁኔታ [illegible] ሕዝብ ንያዎች በአድርባይነት [illegible]ሮ፤ ከአዲሱ ፀረ ሕዝብ ኃይል ጋር በጥቅም በተሳሰረ ኖሮ፤ ከሁለት ዓመት ወዲህ በአብዮቱ ስም የተደረጉትን ፀረ ሕዝብና ፀረ ኢትዮጵያ ክብር ድርጊቶች በአብዮትና በብሄራዊ ነፃነት ስም በግንባር ቀደምነት የሚ[illegible]ም ኃይል ቢሆን ኖሮ "የተሰውትን ጓዶች አርማ አንስተን እንቀጥላለን" ያልነበትን ቃል ኪዳን ምንና በከዳን ነበር?

ይህ እንዳይሆን መኢሶን እርምጃው የሚያስከትለውን መስዋዕትነትና ችግር አውቆ፤ ፈቅዶና መዝኖ በመቀበሉ የአብዮታችንና የኢትዮጵያ እናታችን ክብር የሚጠይቀውን እርምጃ ወሰደ:: በአብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎች ሁሉ ደርግ በአብዮቱ ስም ከሚያመለክተው የቀለበሳ ጎዳና ሌላ አማራጭ፤ ሌላ የሃቀኛ አብዮት ፋና እንዳለ መኢሶን ማንኛውንም መስዋዕትነት እየተቀበለ ማስተጋባቱንና ማሳየቱን ቀጠለ:: ደርግና አድርባይ ድርጅቶች አብዮትንና የእናት አገራችንን ነፃነት ይዘው ወደመቀመቅ በማምራት ላይ መሆናቸውን፤ የአብዮትና የእናት አገር ክብር ጎዳና መኢሶን የሚያመለክተው መሆኑን ሕዝቡ የተገነዘበው ሃቅ ከመሆኑም ሌላ ዛሬ በነዚህ ሁለት መሥመሮች መሃከል ይካሄድ የነበረውን ትግል ፍና ፍና መስከ ስንመለከት መኢሶን ያመለከተው መሥመር ምንኛ ትክክለኛ እንደነበር በማያሻማ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል::

አዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በአብዮቱ ስም የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ቢረግጥ መኢሶን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች አሁኑኑ" ብሉ ከሰፊው ሕዝብ ጋር የትግል አርማውን አነሳ:: የኢትዮጵያ አብዮት በደረሰበት ደረጃ የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ ካልተወቁ ከእንግዲህ ወዲያ እንጂ ወደፊት እርምጃ እንደማይገኝ አስታወቀ:: በሃገሪቱ የተፈጠሩት የሰፊው ሕዝብ የእዲሱ ሕዝባዊ ስልጣን ጥንስስ የሆኑት ሕዝባዊ ድርጅቶችና የበሰበሰው ቢሮክራሲ እንደዚያ በተጣጠበት ሁኔታ ትግሉ እንቶ እንቶን ሲያጠፋ ስለማይበርዱ ሕዝባዊው ስልጣን ፀረ ሕዝቡን ቢሮክራሲ እንዲደመስስ ዲሞክራሲ ያስፈልገዋል ሲል መኢሶን በቆራጥነት ታገለ:: ይኸ ካልሆነ ሕዝባዊ ድርጅቶች ተበቀቀ እንደሚጠወልጉ የእድሃሪው ቢሮክራሲ አሽንጉሊት እንደሚሆኑ መኢሶን ተናገረ:: ዲሞክራሲያዊ መብቶች መታፈናቸውን ቀጠሉ:: በዚያው ልክ ደግሞ አድሃሪው ቢሮክራሲ አይሉ ዛሬ ከነመሊሠማ አንስቶ ቀበ

ሊጎች፣ የገበሬ ማህበራትና ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች "ሕዝባዊነታቸው" የወደመበት ደረጃ ደረሱ::

ዲሞክራሲ ከሌለ "የተራማጆች ህብረት" የሚባለው ቅጥፈት መሆኑን፣ ያለ ዲሞክራሲ ሃቀኛ ሕብረት ለመመሥረት አለመቻሉን መኢሶን ተናገረ:: እኢሩ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት ዲሞክራሲን ማፈን ቀጠለ:: ልዩነቶችን በዲሞክራሲያዊ ውይይት መፍታት ያልቻለው "ኢማሌዴህ" ዝቀ በለገ አገደምና የው ከፍተኛ ኪሣራ ላይ ወድቆ ተገሸ ከተንገዳገደ በኋላ ዛሬ ወርዶ መፍረሱ በይፋ ተነገረለት!

ዲሞክራሲ ከሌለ የብሄረሰቦች ችግር እየተባባሰ ይሄዳል እንጂ ለኢትዮጵያ አንድነት መፍትሄ የሚሆን ምንም ነገር ደርግ ከያዘው ትምክህተኛ ፖለቲካ ሊወጣ አይችልም ያለው መኢሶን ነው:: የሚደረገውን ትግል መላ ለብሄረሰቦች የተሟላ እኩልነትና ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አንድነት በጠር ኃይልና በትምክህተኝነት መሠረት ላይ የተገነባው ያየት አንደሌለበት አስገነዘበ:: በዚህ በኩል የኋሊት እንጂ ወደፊት የደርግ ፖለቲካ የኢትዮጵያን ሕዝቦች አንድነት አናግቶ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ገልጽ ነው:: አንጓላረገደን ከአድሃሪ ኃይሎች ጋር እንታረቅ፣

እጊሩ የቀኝ ኃይሎች ህብረት የውጭን ጠላት ለመቋቋም ከአድሃሪ ኃይሎች ጋር እንታረቅ፣ ሁሉም ነገር ወደጦሩ ግንባር እያለ የቀለበሰ ፖለቲካውን ሲደረድር በመኢሶን ግንባር ቀደም ነት የሚገኙ የሕዝብ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጭቁኖች "ዐርቅ አንፈልግም ተጥቁ!" "ቢሮክራሲው እያዘዘ ይዘምቱበት" "እናት ሀገር ወይም ሞት" በለው ተሰለፉ:: የቀኝ ኃይሎች ህብረት የያዘው ጉዳይ የርስበርስ የሃገሪቱን ድንበሮች ለማስከበር ቢችልም በምንም መልኩ ግን የኢትዮጵያን አብዮት ከቀለበሰ የሚያድን ጉዳይ አልነበረም:: ይህ ፖለቲካ በጦር ነት ዓይነት የኢትዮጵያ አብዮት ከቀለበሰ የሚያድን ጉዳይ አልነበረም:: ይህ ፖለቲካ በጦር ነት ግርግር ፀረ ሕዝብ ኃይሎችን ጠፍ ቦታ የሚያስይዝና የሚያጠናክር ፖለቲካ ነበር:: መኢሶን ያራመደው የፖለቲካ መሥመር ግን የሃገሪቱ ሀብትና አብዮታችንንም የሚያድን ፖለቲካ ነበር:: እጊሩ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት የተከተለው መሥመር የሰጠው ውጤት መኢሶን "የተነበየው" ውጤት ነበር:: "አያዝምቱ ይዘምቱበት" በተባለው በአድሃሪው ቢሮክራሲ አማካኝነት በሚገኙ ጦርነት ለሰው ኃይል ድንበርን አገሪቱን ለመከላከል አልተቻለም:: አድሃሪው ቢሮክራሲ በግርግር በያዘው ቦታ በመጠቀም በሚኒስቴሩ ውስጥም ሆነ በሚሊሺያው ውስጥ ገንብቶ ቀደም ተራማጆችን እየለቀመ ወጣቱን፣ በጠቅላላው በጦርነት ጥረት ላይ ይህ ነው የማይባል አሻጥር እየፈጸመ የሃገሪቱን ችግሮች ማባባስና ሁኔታውን ለቀለበሰ ጭፍጨፋን ቶሎ በጦሩ ግንባር ይልቅ ይፈልጋል ማለት ዘበት ነበር! በመሆኑም ደርግ የአድሃሪውን የሚሊቴሪ ቢሮክራሲ አሻጥር ለመገንዘብ በዛም ጊዜ አለወሰደበት:: ግን ታዲያ ይህንን ተገንዝቦ ወደሕዝቡ ወደ ዛሬው መሥመር ተመለሰ? የለም:: ይህንን ከማድረግ ፈንታ፣ ለጦርነቱ አስፈላጊ የሆነውን አብዮታዊ አመራር በማስገኘት ፈንታ፣ "አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" እያሉ ለእናት አገራቸውና ለአብዮታቸው ለመሞት የተዘጋጁ በሺህና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እያሉ ደርግ በአድሃሪው ቢሮክራሲ አሻጥር የተነሳ በየግንባሩ ለተፈጠረው ችግር ያገኘው መፍትሄ የውጭ ጦር ወደ ሃገሪቱ አስገብቶ ጭፍጨፋና የሃገራችንን ክብር ማስደፈር ነበር! አድሃሪው ቢሮክራሲ ሊያዘምት አልቻለም:: ግን ደግሞ የሱን አሻጥር ተቋቁሞ በከፍተኛ ወሰ ዋዕትነት ይልቅ በተዋጊው መደበኛውና ሕዝባዊ ሠራዊት ላይ፣ የፈላጭ ቆራጭነት ቦታ ይዞ የወጣው ይኸው አድሃሪው ቢሮክራሲ እንደሆነ ገልጽ ነው:: መኢሶን ቀደም ሲል ደርግ የተከተለው "የብሄራዊ ዐርቅ" ፖለቲካ ዞሮ ዞሮ አብዮቱ የሚያስቀለብስ አደገኛ ፖለቲካ ነው ያለው ለዚሁ ነበር:: ይህ ደግሞ ዛሬ ለማንም ገልጽ ሆኖ የሚታይ ሃቅ ነው::

እጊሩ የቀኝ ኃይሎች ህብረት የተከተለው በውጭ ኃይሎች ላይ የመተማመን ፖለቲካ አገሪቱን ሕብረት አመኖክሮ በፀረ ዲሞክራቲክ ገጽታው እንዲገፋበት፣ "ከነፃነት ከተደራጀና ከታጠቀ ሕዝብ ትግል" ፈር የደረሰውን ማፈናፈን እንዲቀጥል፣ ለሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ማለት የደረሰውን ፈሪ ሥራ በሱ እንዲይዘው የሚያገዝ፣ ሁለተኛ ደግሞ አገራችንን በሃያላን መንግሥታት በተራ ቴቲያዊ ገበጣ ጨዋታ ወደ ተራ ጠጠርነት የሚያወርድ፣ በሄራዊ ነፃነታችንን አስደፍሮ በዓለም ሕዝቦች ፊትና በተለይ በአፍሪካ ሕዝቦች ፊት እንደገና "የአህጉር ሃፍረት" የሚያደርገን ሁኔታ የሚያመጣ አደገኛ ፖለቲካ መሆኑን መኢሶን ተናገረ:: በሱ ፈንታ የአብዮትን ችግሮች ለመወጣት እርግጥ የውጭ እርዳታ ያስፈልጋል ግን ከሁሉ በላይ የሕዝቡ ድጋፍ፣ መደራጀትና መታጠቅ ላይ መተማመን እንደሚያስፈልግ፣ እርዳታው ከዚህ የአብዮት ጉዳና የሚያርቅ እርዳታ እንዳይሆን፣ በእርዳታ ስበብ ብሄራዊ ነፃነታችንም እንዳይደፈር፣ እርዳታ በእኩልነት እንጂ በወገንነት ደረጃ መቅረብ የለበትም ሲል ተከራከረ:: የደርግ ፖለቲካ በሁለቱም በኩል ዛሬ የት ላይ እንደጣለን ገልጽ ነው::

በዚህ ዓይነት በብዙ መቀጠል ይቻላል:: ባጭሩ ለማስቀመጥ ግን ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮትና የሃገሪቱ ብሄራዊ ነፃነት የሚገኙበትን መቅኖ የተመለከተ ሰው መኢሶን ያራምደው የነበረውና አሁንም የሚያራምደው መሥመር ምን ያህል ትክክለኛ እንደነበር በቀላሉ ሊረዳው ይችላል:: ይህንን ምንነው ከዛሬ ሁለት ዓመት ጀምረን ባነሳናቸው ከደርግና ከአድርባይ ድርጅቶች ወራዎች ጋር በነበረን ልዩነቶች የሰፋ አመንጭ ትክክል ነበር ብለን "ታሪክን" ለመጥሩ አይደለም:: መኢሶን አንስቷቸው የነበረት ጥያቄዎች አሁንም የአብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው:: አሁንም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያቀርባቸው ናቸው:: ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ የነዚህን ጥያቄዎች ትክክለኛነት፣ ሕዝቡ በመኢሶን ቀስቃሽ ብቻ ባይሆን በተጨባጭ በሚያውቀው በሚያየው ተረድቷል:: ስለሆነም ዛሬ ሰፊው ሕዝብ የሚፈልገውን ያውቃል:: ግን በአብዮት ሠፈር እንደቀድሞ፣ ከአብዮት ተገንጥሎ ወደ ታሪክ እተላነት በመንጎድ ላይ እን

ደሆነ ያውቃል::

ይህ የፖለቲካ ጥሬት ደግሞ በቀላሉ የሚደፈርስ አይደለም:: እንዲያውም በመጭው ጊዜ በዚህ በኩል ይበልጥ ጥሬት እየተገኘ ይሄዳል:: ለምን? ምክኒያቱ አጭር ነው:: እጊሩ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት በመደብ ይዘቱ የተነሳ የኢትዮጵያን አብዮትና የሃገሪቱን ብሄራዊ ነፃነት ለማስለከተት ጥያቄዎች ለአገደፍ ቸውም ተገቢውን መልስ ለመስጠት ከዕለት ዕለት ነፈነት ለማስለከተት የተገነጠ አገደሚሄድ ከአነሶ "ለመተገበይ" ይችላል:: በዚህም የተነሳ ይህ ይበልጥ እየተካነው እንደሚሄድ ከዕለት ዕለት በአድሃሪው ቢሮክራሲና በውጭ ኃይሎች ቁጥጥር ስር እየገባ የሚሄደው "ህብረት"... ጠጠቀሰሳው በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ፀንተው ከቆሙ ኃይሎች ጋር በሙሉ ከዕለት ዕለት የባሰውን እየተቆራረጠ፣ የባሰ ቀራኒ ውስጥ እየገባ ይሄዳል:: በዚህም የተነሳ ከገባበት አዙሪት ውስጥ ለመውጣት የሚቀረው መንገድ የባሰውን ከቢሮክራሲውና ከውጭ ኃይሎች ቁጥጥር ስር መውደቅ እንደሆነ ገልጽ ነው:: ባለፉት ወራት ከመኢሶን አባላት ሌላ በተዉማሪ ከወዝአደር ሊግ፣ ከሌኒሶኢት፣ ከሰደድ ከራሱ እንዱ ክፍል ጋር እየተፈጠመ የሄደው ቀራኔ የኢትዮጵያን አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያልቻለው የቀኝ ኃይሎች ሕብረት ይበልጥ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ቁጥጥር ስር እየወደቀና በሃገሪቱ ባሉ ተራማጅ ኃይሎች ጋር እየተባባሰ የሚሄደው ቀራኔ ውስጥ እየወደቀ መሄዱን የሚያሳይ ሂደት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ መጭው ጊዜ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ለተሰለፉ ኃይሎች ለትግላቸው ይበልጥ ምቹ እንደሚሆን የዚያኑ ያህል ገልጽ ነው:: መጭው ጊዜ ለዲሞክራሲ፣ ለብሄረሰቦች እኩልነት፣ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ክብርና ነፃነት፣ ለሃቀኛ የተራማጆች ህብረት... ለሚታገሉ ኃይሎች እንጂ ለፀረ ዲሞክራሲ፣ ትምክህተኝነት፣ ለብሄራዊ ውርደት ለቆሙ ጥቂቶች እንዳይደለ ባይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው:: ስለሆነም የኢትዮጵያ ተራማጆች በጠበቀትና ባልተገረጡበት የገባስ ከበርቴው መደብ መንሸራተት በምንም ዓይነት ሳይሸበሩ፣ በአቋማቸው ትክክለኛነት ብቻ ሳይሆን በዚህ ትክክለኛነት ዘላቂነት ሙሉ በሙሉ በመተማመን ጊዜ ለእነሱ እንጂ ለተንሸራታቶች እንዳልሆነ ለማወቅ፣ የታሪክ ሂደት ለእነሱ እንጂ በቀ ለባሽ በኩል እንዳልሆነ በመረዳት ለመጭው የትግል ምዕራፍ በጥሞናና በዲሲፕሊን፣ በቀራጥነትና በመጭው ደረጃ በሚደጠራመር መንፈስ ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው:: ይበልጥ ለታሪክ አተላዎች እንጂ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንደሆነች፣ ሕዝባዊት ኢትዮጵያ እንደሆነች፣ የተ[illegible] ነፃ ኢትዮጵያ እንደሆነች፣ ከአብራኳ ከም ፈጥጣቸው ታጋይ ልጆቿ ተገልና ደም በፊውዳሊዝም፣ በኢምፔሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም መቃብር ላይ ትገነባለች::

ይህንን ስላልን መጭው ጊዜ አስቸጋሪ የትግል ጊዜ አይሆንም ለማለት አይደለም:: የፖለቲካ ጥሬት በቻውን ፀረ ሕዝቦችን ተቋቁሞ ድል አያደርግም:: ግን ይህ ራሱ በኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ኃይሎች እጅ ያለ ከፍተኛ የትግል መሣሪያ ነው:: በነሐሴ 1969 ዓ. ም. የትግል ስልት ለውጥ ባደረገበት ሰዓት በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሚከተለው ብሎ ነበር:: "የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለነፃነትና ለእኩልነት፣ ለሰላምና ለወደፊት እድገት የሚያደርጉት ትግል ድል እንደዛሬ እንደ ሁኔታ አገኘቶም አያውቅም:: ችግሮቻችንና ጨከመቶቻችን፣ የአብዮታችን ጠበቆችና የሃገራችን መወረር ጊዜያዊ ናቸው:: ዘላቂነት የላቸውም:: የፖለቲካ መሥመር ትክክለኛነት ወባጊ መሆኑን በመገንዘብ፣ ፖለቲካን አስቀድመን ችግርንና ቆትን ባገፈራ በሰፊው ሕዝብ ተዋፋነት አስከመጨረሻው ለመታገል ቆርጠን ከተነሳን፣ አንድነታችንን አጠንክረን ወደፊት ከተራመድን የፈደውን ጊዜ ቢፈጅም የፈለገውን መስዋዕትነት ቢጠይቅም ብርሃን እናሸንፋለን"::

ይህ እንደተገለጸው ሙሉ በሙሉ ትክክል ነበር:: ግን አሁን አብዮት ለማራመድ ምን ያህል ትክክለኛ አቋም ቢይዙ አቀም ያስፈልጋል:: ዛሬ ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲያውም አንገብጋቢ የሆነው ጥያቄ አስከዚህም ለሰፊው ሕዝብ የትግል አቀጣጫዎችንና ዓላማዎችን መጠቆም ሳይሆን በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘውን መሥመር ከሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን ኃይል መሰብሰብና ማደራጀት ነው ብለን እንገምታለን:: የቀኝ ኃይሎችም ይህንን ያውቁታል:: የትግል መሣሪያ የሆኑትን ድርጅቶቻችንም በሙሉ ያፈራረሱት፣ ግንባር ቀደም አገልጋዮቻችንና አደራጆቻችን በሙሉ የረሸኑበትና በየእሥር ቤት ያጐሩበት፣ ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶቻችን ለማፈን የሚከረበት ዋናው ምክኒያትና ከዚያም "ተገለህ ውረድ" በለው ያሸፈነት ለዚህ ነው:: የቀኝ ኃይሎች ይህንን የፖለቲካ ጥሬት ማደፍረስ ስላቃታቸው፣ ይህ መሥመር ከሥራ ላይ እንዳይውል በዚህ ቀላል በሆነው የመደራጀት ጥያቄ ላይ ተረባርበዋል:: ተራማጆች ደግሞ በፖለቲካው መሥመር ጉዳይ ባገኙት ድል ላይ ተመሥርተው በዚህ ቀላል ጥያቄ ላይ መረባረብ አለባቸው:: የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ይህ ነው::

አወን! ዛሬ የሃገራችንን ሁኔታ ሌላ መልክ የሚሰጠው ባለው እኩን አመቺ በሆነና <u>ከዕለት ዕለት ለአብዮታዊያን ይበልጥ አመቺ እየሆነ</u> በሚሄደው የፖለቲካ ጥሬት አንፃር ቢታይ ይህንን ፖለቲካ ከሥራ ላይ ሊያውለው የሚችለው ኃይል ሁኔታው በሚጠይቀው ልክ አለመደራጀቱ ኃይሉን አለማሰተባበሩ ነው:: በዚህም የተነሳ የጊዜው ዋና አንገብጋቢ ጥያቄ የግንባር ቀደም ድርጅቶች ኃይላቸውን ማጠናከርና ተራማጆች በቀኝ ኃይሎች ሕብረት ቢሯና ተገኩለ የተበታተነውን ህብረታቸውን እንደገና መገንባት ነው እንላለን:: ይህንን ተግባር በዚች ቀራችን ሁለተኛ ክፍል እስከንመለከት ድረስ ዛሬ በድርጅት ጉዳይ ያለንበትን የመነሻና የመጨረሻ ሁኔታ መመልከት ይጠቅማል::

እንደማገናኛውም መስከ በቀኝሃይሎች ሀብረት ቢራ የተነሣ በዚህ በድርጅትም መስከ የተገኙት ዉሎች ሁሉ ተበትነዋል፡፡ የኋሊት ጉዞ ተደርጓል፡፡ ይህ በድርጅት ጉዳና ላይ አገራችን ያደረገቸው የኋሊት ጉዞ ከብዙ አንፃር ሊታይ ይችላል፡፡ በመጀመሪያ በአብዮት በፊር ተደራጅቶ ይገኝ ከነበረው ሃይል ዛሬ ወይ በአመራር የፖለቲካ ከሥረት የተነሳ ተሰሩ እየቀረጠም ሆነ በቀኞች እየተመታ በመበታተን ላይ ይገኛል፣ ወይ ደግሞ በጠራና ግልጽ በሆነ አብዮታዊ መሥመር ተሰልፎ በከፍተኛ ፀረ ህዝብ አመፅ የተነሳ ድርጅቶች ተዓከመዋል፡፡ ከዚህም ከአመራሮች የፖለቲካ ክሥረት ከተከተለው መበታተንና በፀረ'ህዝብ አመፅ ከተከተለው ድርጅታዊ መዓከም ጋር ተያይዞ ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም ደርሰውበት የነበረው የህብረት ደረጃም ተቀልበበ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ የተነሳ ዛቅ በሰነ·እንደምናየው "ኢማሌዲህ" ይባል የነበረው የህብረት መዋቅር ጠርቡ ከመደምሰሱ በፊት የቀ ላይ "ማርክሲስት ሌኒንስት" የሚለው ላይ "የድርጅቶች ህብረት" ሊባል እንደሚችል የማይታወቅበት ግንድ የሆነ የክሥረት ደረጃ ላይ ወድቆ እንደነበር እናያለን፡፡

የተለያዩ በአብዮት በፊር የነበረትንም ሆነ ያሉትን ድርጅቶች ሁኔታ እንመልከት፡፡ እዚህ ላይ በአንድ በኩል የ"ግራ" አድርባዮና የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ሁኔታ አለ፡፡ የነዚህ ድርጅቶች አመራሮች ተራ በተራ የተከተሏቸው የከሰረ የፖለቲካ መስመሮች ነበሩ፡፡ በዚህም የተነሳ ዉሎ ይደር እንጂ ሁሉም ከፖለቲካ ክስረታቸው ጋር የተያያዘ ድርጅታዊ ክስረትና መበታተን መፍረከረክ ደርሰባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬም ቢሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እንዲገበው የሚታገሉለትን የፖለቲካ መሥመር በግንባር ቀደምነት እንስቶ የሚቀጋው መኢሶን አለ፡፡ መኢሶን የተከተለውና አሁንም የሚከተለው ፖለቲካ የህዝብ መሥመር ነው፡፡ የፖለቲካ ኪሣራ የለበትም፡፡ ስለሆነም በፀረ ህዝብ ሃይሎች የተበነዘረበት አመፅ ድርጅታዊ መዓከምን እንጂ ኪሣራን ሊያመጣበት አይችልም፡፡ አላመጣበትምም፡፡ ፖለቲካውና መስመሩ ትክክለና ስለሆነ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ማርክሲስቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶችም እንደሱ ዲሞክራሲ፣ ብሔራዊ ነፃነት፣ የብሔረሰቦች እኩልነት፣ ሃቀኛ የተራማጆች ህብረት...ስለሚሉ ለጊዜው ሁኔታ መቀቅሬን አስተካክሉ ወደፊት ይጋዛል እንጂ መንም አይነት አመፅ ሊደመስሰው አይችልም፡፡

በመጀመሪያ ከፖለቲካ ኪሣራ ጋር ድርጅታዊ ኪሣራ የደረሰባቸውን እንመልከት፡፡ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እንደተወሳው የኢሕአፓ ቺብደኞች ትግል በኢትዮጵያ ተራማጆች በተለይም በወጣቱ አካባቢ ያስከተለው እጅግ አስከፊ የሆነ ውጤት አለ፡፡ ኢሕአፓ የኢትዮጵያን አብዮት የበደለው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ተራማጅ ኢትዮጵያውያንን መጠረሩ፣ በሃቅና በጥሞና የሚካሄዱ ትምህርታዊ ውይይት እንዳይካሄዱ አፍና እንዲ ታጋይ ትውልዱን አደንቁር በቀልበሽ

ፖለቲካው ለማበለፍ መፍጠርጠራ ብቻ አይደለም፡፡ ዛሬ እንደምናየው መሰሪቸው የተከተሉት ሃቀኛ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን፣ በከንቱ ተጨፍጭፈው ያለቀትም፣ የኢሕአፓ ክሥረት በምንም አይነት በማያወላውል ሁኔታ ይፋ ሰጣ የወደቀበት ዉዥንብርና ተስፋ መቁረጥ፣ ምን ሃቀኛ መሥመር ቢኖር ከሱ ሥር ለመሰለፍ የሚያበቃት ከፍተኛ ጥርጣሬና ማመንታት በጠቅላላው ለፖለቲካ ትግል የማያበቃት ገለልተኝነት፡.. የኢሕአፓ መሪዎች በኢትዮጵያ ታጋይ ትውልድ ላይ የፈፀሙት ታሪክ ምን ጊዜም ይቅር የማይለቸው ወንጀል እንደሆነ ለማየት አያስቸግርም፡፡

የኢሕአፓ ቀልበሽ የፖለቲካ መሥመርና ጀብደና የትግል ዘዴ ካስከተለው መበታተን ሌላ ከአንድ አመት ወዲህ ደግሞ የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች አመራሮች የተከተሉት ፖለቲካ ያመጣው ውዥንብርና ድርጅታዊ ክሥረት አለ፡፡ የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች መሪዎች የከሠሩና የኢትዮጵያን ጭቁኖች እንገብጋቢ ጥያቄዎች የሚፃረር የፖለቲካ መሥመር ተከትሎ፡፡ ይህንን መሥመራቸውን የተቃወሙትን ሃቀኛ አብዮታውያንን ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር አብረው አሳደዱ፡፡ አዋጡዋቸው አስያዙ፣ አስገረፉ፣አስረሸኑ፡፡ ፀረ ህዝብ ፖለቲካቸውን በወገኑ መልክ "ህዝቡ አባሯራው፣ ህዝቡ ይደግፈናል" እያሉ በረሃዎና በጋዜጣ አስለፈፉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ፖለቲካቸው ከሥራዩተነሣ ህዝብ እንደተፋቸው፣ ህዝብ ከተፋቸው በኋላ ደግሞ በአሸዋ ላይ የገነቡት "ድርጅታዊ ቤታቸው" ፀረ ህዝቡ ቢሮክራሲ "እፍ" ሲለው እንደሚፈርስ አልተገነዘቡም ነበር፡፡ ነገር ግን ተጠቅመባቸው ከጨረሰ በኋላ አድሃሪው ቢሮክራሲ እንደደረቀ ሎሚ ጣላቸው፡፡ አምና ይከተሉት የነበረው ዲሞክራትና አገር ወዳድ፣ አድርባይ መሪዎች በምን ላይ ከፀረ ህዝቡ ቢሮክራሲ እንደተሰለፉ ሳይገባው እየታደነ ይመታ ጀመር፤ መኢሶን በጭቁኖች በመታ "ዲሞክራሲ" ብሎ ነው፡፡ መኢሶን የትምክህተኞች አመፅ በወርደበት "የብሔረሰቦች እኩልነት" ብሎ ነው፡፡ ... ባጭሩ ፀረ ህዝቦችና ፀረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ቢያጠቁት በግልፅና በይፋ ከህዝቡ ወገን መሆኑን አረጋገጠ ነው፡፡ በአድርባይ ድርጅቶች ሥር ተደራጅቶ የነበረው ሃቀኛ ታጋይ በአንፃሩ አይነቱ ሁኔታ ከላይ መሪዎቹ በሚያካሂዱት የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት እሱም እየተመታ ሲሄድ ሙሉ በሙሉ ግራ መጋባት ምንም የሚያስገርም አይደለም፡፡ ግራ መጋባት ብቻ ባይሆን ለዚህ ክፍል ትግልም ልዩዋል ቤል አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነው፡፡ የአድርባዮቹ ድርጅቶች አመራሮች ያስጠበቁትን የከሠረ የፖለቲካ መሥመር ይዞ ወደ ህዝቡ ሊሄድና ሊያደራጅ አይችልም፡፡ ያለው አማራጭ ሃቀኛውን መሥመር እንዲሠተ የህዝቡን እንገብጋቢ ጥያቄዎች ይዞ ከሌሎች አብዮታውያን ጋር በአንድነት መቆም ብቻ ቢሆንም ይህ በአድርባይ ድርጅቶች ውስጥ የነበረው የሃቀኛ ታጋዮች ክፍል ከፀረ ህዝብ ሃይሎች በኩል በወረደበት

ግብአቱ ገና ገራ ከማጋበት ደረጃ አልፎ፣ በወዝንበር ውስጥ ከመጥዛቅ አልፎ አለ ሄደም:: በዚህም የተነሳ ዛሬ በተለይ "በወዝአደር ሊግ" ውስጥ ተሰልፈው የነበሩ ታጋዮች ብቻ ሳይሆኑ በአብዮታዊ በደይ በራሱ ውስጥ የሚገኙት ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በአመራር ስህተቱና አደርባይነት ባጋጠማቸው የፖለቲካ ከሥረት ጋር ከፍተኛ ድርጅታዊ ከስረት ውስጥ ወድቀው ይገኛሉ::

ከዚህ ሌላ እንገኘህ የተገከደው መሰረገ ድርጅታዊ መደከም አለ:: በሺህ የሚቆጠሩ አባላቱ ታሥረውበት፣ በመቶ የሚቆጠሩ አባላቱ በያለበት ወድቀውበት እንኳን እንደና ዓይነቱ ለጋ ድርጅት ይቅርና ማንም ድርጅት ቢሆን ወዳከሙ አይቀርም:: ነገር ግን ሁለት ነገሮች አሉ:: መሰረገ የሚከተለው መሥመር ሕዝባዊ በለሆነ ምንጊዜም ቢሆን ድርጅታዊ ኪሳራና መበተን ሲደርስበት አይቸልም:: ይኸንን ደግሞ ባለፈው አንድ ዓመት ዘኩል የአብዮትን ሂደት በሚገባ አሳይቶታል:: እንዲ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት በአደርባይ ድርጅቶች "ገንባር ቀደምነት" በመጀመሪያ መሰረገን ከሕዝቡ ለመነጠል ሞከረ:: የመሥመር ትግል ብሉ የጀመረው የራሱን ኪሣራ ማጋለጥ ሆነ:: መሰረገን ከሕዝብ መነጠሉ ፖለቲካ አልሠራም:: ድርጅቱን ለመከፋፈል ሞከረ:: ስለ አሁን "ከወዝአደር ሊግ" ድርጅት ላይና ሰሞኑ እንደሚታየው በሰደደም ውስጥ "ገራ ከንፍና" ያን ከንፍ እያለ እንደጀመረው አድሃሪው ቢሮክራሲ በመሰረገም ውስጥ "ገራ ከንፍ" አገኘሁ ብሎ ተሳምዶ ነበር:: "ገራ ከንፍ" የተባለቸው ነገር እንኳን ከንፍ ለተቃለ ቀርቶ በበረቀን በክሉ የሬገሬቸ የታሪክ ስቀላ ሳቢ ሆና ተገኘለች:: ይቺ "ገራ" ከንፍ ቢላት ቢላት ከአበር ሰው አለበለጠቸለትም:: ማንንም አላተለለቸለትም:: እንገኘህ ይኸ አለሠራ ቢል በደርጅቱ ላይ በሰየለት ፀረ ሕዝብ አወጅ ተሰማራ:: ከላይ እንዳልነው በዚህ አወጅ የተነሳ ንቅናቄያችን ተጎዳ:: ግን አልተደመሰሰም:: በፖለቲካው አንፃር በሃቀ ለአብዮት፣ ለሕዝብ፣ ለእናት አገር ባደረገው ምርጫ እስከመጨረሻ የሚሰዋ ድርጅት መሆኑን በሰፊው ሕዝብ ፊት አስመሰከረ:: በነዚህ ጊዜያቶች ደምና ሥራ መሰረገ የጻፈረው የትግል ታሪክ በሕዝብ ዘንድ ተናግይነቱን መሰረለት:: በድርጅታዊ የገጠሬ በኩል ደግሞ ለዘለዓለም ትግሉ በውድ ጊዜያቶች ደምና ሥራ እየከፈለ የቀሰማቸውን ትምህርቶች በሚገባ አዋህዶ በአብዮቱ ሠፈር ወታገሩን ነው::

ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት በመኢሶን ግንባር ቀደም ታጋዮች ተከሸ ላይ የወደቀ ኃላፊነት ብቻ አይደለም:: ዋናው ኃይል በሚሊዮን የሚቆጠረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: ይህንን ኃይል ለማንቀሳቀስ ደግ ብቻ ሳይሆን በግንባር ቀደምነት የተሰለፉ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፣ ሠራተኞችና አገር ወዳጆች ተግባር መሆኑን እያገናኙ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ፣ እያገናኙ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊት አምነው መቀበል አለባቸው:: ለዲሞክራሲ፣ ለእኩልነት፣ ለብሄራዊ ነፃነት የቆሙ ኃይሎች ሁሉ ዛሬ ጉልቻቸውም ጊዜ ይበልጥ የወደቀበትን ወዝንበር ነውንተው፣ የፀረ ሕዝቦች አወጅም ሆነ የተለያዩ አደርባይ አመራሮች የከሰረ የፖለቲካ መሥመር ያመጣባቸውን ድክታትን አሸንፈው በሃቀኛ መሥመር ላይ ለእናት አገርና ለአብዮት በህብረት መቆየት አለባቸው::

የዛሬው፣ የመኢሶን የህብረት ጥሪ ይኸ ነው:: ወዝንበር ይበቃ፣ መበታተን ይበቃ፣ በሁሉ በኩል ለአብዮታችን፣ ከሁሉ በፊት ለእናት አገራችን የምንል ኢትዮጵያዊያን ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደፊት እንራመድ ይላል:: እንግዲ ይኸንን ሊሳ የተራማጆች ጥሪ ለናስተገባ "ኢማሌድህ" ብሎ ይጠይቀን ይሆናል:: በደፈ ከመፍረሱም በፊት ቢሆን "የወዝአደር ፓርቲ የገበሰ" እየተባለ ይተረተለት የነበረው "ኢማሌድህ" የካቲት 1969 ዓ.ም. "ኢማሌደህ" አለነበረም:: ከዚያናው ጋር ቢነጻጸር ከላይ እንደጠቀስነው "ኢማሌድህ" ይባል የነበረው ህብረት" የገደ ኪሣራዎች ደርሰበታል::

የመጀመሪያው የ"ኢማሌድህ" የፖለቲካ ከሥረት ነው:: አንዱ ድርጅት ወይም ራሱ ማርክሲስት ሌኒኒስት [illegible] ብሎ ብቻ "ማርክሲስት ሌኒኒስት" ነው ማለት አይቻለም:: በኢማሌድህ የፖለቲካ ከሥረት በውስጥ [illegible] በየካቲት ድርጅቶች የፖለቲካ ከስረት ጋር የተያያዘ ነው:: ይኸንን ከሠረታቸውን ለማሳየት ሌላ ዝብዝብ ውስጥ ከመግባት እነዚህ "ማርክሲስቶች" "ይኸ ዝቅተኛው ነው ከዚህ ክስረት አንጻርሰን" ይሉት የነበረውን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አንዳንድ አደርገው ምንጠርጠረን እንዳወጡት መጠየም፣ ከዚያስ ወዲህ የየካቲት 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ህብረት የጋራ መግለጫና ወርሃ ገብር ላይ ከማሉበትና ከተገዘቡበት እንዳማቸው የተናውን እንዳከበሩ ሊሰገ መቆየት ብቻ ይበቃል::

ሌላው ደግሞ ኢማሌድህ ላይ የደረሰው ድርጅታዊ ከሰረት ነው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢማሌድህ የሚባለው ነገር የት ላይ "የድርጅቶች ህብረት" እንደሚባል ገራ የሚያጋብ ነበር:: መሰረገ እንደሆነ "ተባረረ" ሊዋሐድ እንደሆነ "ሊገባ" ተወገደ፣ "የወዝአደር ሊግ" እንደሆነ የአድሃሪው ቢሮክራሲ ሹማምንት "ገራ ከንፍ" ተብለው አመራረን ከያዙ በኋላና ሰሞኑ ሁሉ እየተፈረሰ በአስር ቢሮ ከታገረ በኋላ ምን ቀርቶ ነበረ "ህብረት" አብለ እንደሆነ አይታወቅም:: እንዲሁ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በየካቲት 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ለትግሉ ያላቸው ወሣኔያ እንዲሆና የው በጋራቸው ከፍለው ያቋቋሙትን "ኢማሌድህን" ቀቀትን እዚህ ላይ አሳየም:: አድሃሪው ቢሮክራሲ ለደፈግን ራሱንም ቢሆን የሚፈለገው አብዮቱ በም እየማለ ለማያደርገው ጥፍጠፋ "ሽፋን" እስከሰጠው ነው እንጂ ተራማጅን "ከደረሰ" በኋላ ምን ሊያደርግለት "አሽሩሩ" ይለዋል? በዚህም የተነሳ አድሃሪው ቢሮክ

ራሲ "ዘመቻውን" ቀጥሎ አሁን ደግሞ "በደፈጣ በአድሃሪዎች የተገለቀለቀ ድርጅት ነው" በማለት በዚያ ውስጥ ያሉ ሃቀኞችን እየመታ ያፈራርሰው ይዟል:: እርም የነወዝ ሊግ ድርጅታዊ ኪሣራ እየወደቀበት ነው::

በከሣራ ድርጅቶች "አባላት" የተመሠረተ "ህብረት" ደግሞ ያው ኪሣራ በመሆኑ ይኸው በየካቲት ወር 1971 ዓ.ም. የወጣው "የህብረት ደምጽ" ህብረቱ መፍረሱን፣ "ኢማሌድህ" ይባል የነበረው ነገር ራሱ "በአድሃሪያን ስለተገለቀለቀ" ከእንግዲህ እሱን "እየህደ" ፓርቲ ማቋቋም የማይቻል መሆኑን አበስሮልናል:: ለአድሃሪዎች "የኢማሌድህ ታሪካዊ ሚና" አለቀ ማለት ነው:: ከእንግዲህ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በይፋ ከደወ፣ ቢያገባ በዚህ ፕሮግራም ላይ ቆመው የሚታገሉ ድርጅቶችንም ሆነ ግለሰቦችን በይፋ ተደቅቀው የሚታገሉበት በፀረ ሕዝብ ገጽታቸው ደፍረው የሚወጡበት ደረጃ እየደረሱ ነው ማለት ነው:: የየካቲት 1971 የህብረት ደምጽ ይህንን በፀረ አብዮት ጉዳና ላይ የተደረገ አንዱ "የወደፊት እርምጃ" አዲስ ምዕራፍ ብሎ በደመታል::

ይህ "አዲስና ወሳኝ ምዕራፍ" የኢትዮጵያ ወዝአደሮች ፓርቲ "ከድርጅቶች ውህደት" ሳይሆን "ከግለሰብ ኮሚኒስቶች ውህደት" ይመሠረታል ብሉ የኢማሌድህንም ሆነ አወጣጡ ቀርቶ ፍል ጊሉ የነበረትን ድርጅቶች መፍረስ አበሰሯል:: በዚህ "ሂደት" ታሪክ ላይ ወደፊት በሰፊው እንመለሰበታለን:: ይህ "አዲሱ ምዕራፍ" በከሠረ ፖለቲካ ላይ መጋዝ ጀምሮ የነበረው "ኢማሌድህ" ራሱም "ወደወዝአደር ፓርቲነት" በመለወጥ ሳይሆን እንዲሁ <u>በመበተን</u> ወደ ታሪክ ትብያ መጣሉ የጠረደበት ምዕራፍ መሆኑን ብቻ ጠቁመን ለጊዜው እናልፈዋለን::

እንግዲህ የቀደሞ ኢማሌድህ ከሽፏል:: ፈርሷልም:: ነገር ግን ይኸ ብቻ አይደለም:: ይህ ከሥረት ባይኖር እንኳን ኖሮ ኢማሌድህ "የማርክሲስት ሌኒኒስቶች" ብቻ በለነበር ዲሞክራቶችንና አገር ወዳጆችን የሚጨምር ህብረት አልነበረም:: ዛሬ ከመቼውም ጊዜ የኢትዮጵያ አብዮት በቀኝ ኃይሎች ህብረት ሴራ የተነሳ ከገባበት መከራ ወጥቶ ወደፊት እንዲጓዝ የማርክሲስት ሌኒኒስቶች ብቻ ሳይሆን የመቀላለው የተራማጅ ኃይሎች ህብረት ያስፈልጋል:: ዛሬ መሰረገ ከላይ ባቀረብነው የጊዜው ሁኔታዎች ትንተናዎች ላይ ተመርኩዞ ለዚህ ህብረት ጥሪ ያደርጋል::

<u>ክፍል 2.</u> <u>የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ለመላ ኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፣ ዲሞክራቶች፣ አገር ወዳጆች ሁሉ የትግል አንድነት ጥሪ</u>

ጓደኞች፣ ጓዶቻችን፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን!

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የሰፊውን ሕዝብ ወገን መርጦ ለአብዮታችንና ለእናት አገራችን ክብርና ነፃነት በግንባር ቀደምነት ሲዋደቅ የቆየና አሁንም በመዋደቅ፣ በመስዋትና ወደፊት በመራመድ ላይ መሆኑን ዐላፊ በደስታ ጠላት በመርበትበት የሚመሰክሩት ሃቅ ነው:: [illegible] ቢጥለጣጨ በኃይለ ስላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ፣ ከዚያም በየካቲት የዲሞክራሲያዊ [illegible] የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ፈር ለማስያዝ ከሌሎች ታጋይ ኢትዮጵያዊያን ጋር [illegible] አገር ፍቅር የተቀናጀውን ማንኛውንም መስዋዕትነት እየከፈለ በግንባር ቀደምነት ተሰልፎ ዛሬ አሁንም እንደተሰለፈ ይገኛል:: በዚህ ትግሉ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ተራ በተራ የተነሱ ኃይሎች ሁሉ ከተራ ፊውዳል አለቃልቶና ሃሜት እንከተ እስከለየለት ፀረ ሕዝብ አወጅ ድረስ በማፈራረቅ መሰረገም ላይ ተነስተው ሊያጠፉት ሞክረዋል:: ደግሞ እንዳልነው መሰረገ የፖለቲካ እምነቶቹ የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎቶችና ምኞቶች የሚያንፀባርቁ፣ የሃገራችንን ክብር፣ አንድነቷንና በለጸገናዋን የሚያረጋግጡ እምነቶች ስለሆኑ ነገናው ፀረ ሕዝብ ኃይል መሰረገን በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት፣ በግንባር ቀደም ኢትዮጵያዊያን ፊት <u>በፖለቲካ መሥመሩ</u> ሊያጋልጠውና ሊያገለው አልቻለም:: ስለሆነም የኢትዮጵያ አብዮት በመቃወም የተነሱ ኃይሎች በሃቀኛ ተራማጆች ላይ በፀረ ሕዝብ አወጅ ከመሠማራት በስተቀር የገኙት የአብዮትን ሂደት መቋቋሚያ ዘዴ የለም::

ፀረ ሕዝብ ኃይሎች በተለይ ከሁለት ዓመት ወዲህ በአብዮቱ ላይ ያካሄዱት የጥቃት ዘመቻ በመጠኑም ቢሆን ለጊዜውም ቢሆን የአብዮትን በፊር ማስከም የቻለው ተራማጆች መከፋፈል በመቻላቸው ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ገራ ኃይል ወቅላነት ተገቀመው እንዳን በእንቅ ሰሞታ ያደረጉት ጥረት ስለተካከላቸው ነው:: ሠፈራችንን ያስጠያው ለበፋፋ ዎች ብሬ ድርጅታችንን ስጥተን በመገኘታችን ነው:: ከዚህ ሁኔታ ሊያወጣን የሚቸለው በመነከላችን መከፋፈልን አጥፍተን ለፀረ ሕዝቦች መግቢያ ቀዳዳ በንነሳ ብቻ ነው::

"መከፋፈል ይበቃ" ስንል ከሁን ወዲያ ሁሉ እንደመኢሶን ያስብ፣ ሁሉ የኛን መሥመር ሙሉ በሙሉ ይከተል ማለታችን አይደለም:: ለኢትዮጵያ አብዮትና ብሄራዊ ነፃነት በቆሙ የተበጣጠሩ ኃይሎች ማካከል ብዙ ልዩነቶች አሉ:: ወደፊትም ይኖራሉ:: ነገር ግን ከእነዚህ ልዩነቶች በአሻገር የአብዮቱን ሠፈር የሚያያይዙ አንድ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች አሉ:: መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ይፈልጋል:: በመላ ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች እኩልነት ይፈልጋል:: የአገራችን ብሄራዊ ነፃነትና ክብር አይደፈር ይላል... ብሄራዊ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ከሥራ ላይ እንዲውሉ

ይጠይቃሉ:: በነዚህ ዓላማዎች የምንስማማ ኃይሎች ሁሉ መሠረታዊ አንድነቶች አሉን:: በነሱ
ላይ የመርከዝነን እነሱን ከሥራ ላይ ለማዋል በአንድነት ወደፊት መጓዝ አለብን:: በነሱ
ፕሮግራም ከሥራ ላይ በሚውልበት ዘዴ በመካከላችን ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ይህ
በአብዮት ወገኖች መካከል ያሉ ልዩነቶች ናቸው:: ግን እነዚህ
ከበር እስካለን ድረስ፣ አሉስነት፣ አንድነት፣ በለጸገና፣ ብሄራዊ
ነፃነት ለነዚህ ዓላማዎች በሃቀ እስከቆምን ድረስ የኢትዮጵያ አብዮትና ብ
ሄራዊ ነፃነት ጠላቶች በኛ መካከል ቀዳዳ ልዩነት አያዩም! ለፀረ ሕዝብ ዓላማቸው እንዲያመች
ብቻ ቀደም ተከተል ይበላሻል እንጂ ዘር ዘር ለማጠይቅ የሚፈለጉት አብዮትና እናት አገር
የሚለዩንና ለፀረ ሕዝብ ፖሊሲዎቻቸው አላገለግልም የሚለውን ነገር ቀደም ኃይል ሁሉ ነው::

መሊሳን ለመሰ ኢትዮጵያ ተራማጆች ዛሬ የሚያደርገው ጥሪ ከሁሉ አስከፊውን ይህንን
ሃቀ ተገንዝበን ፀረ ሕዝቦች አንዱን ከሌላው እያጋጩ፣ አንዱን ለመምታት በሌላው እየተጠቀሙ
ሁላችንንም ተራ በተራ ለማውደም ለስነዘሩት ሴራ መሣሪያ ከመሆን እንዲቆጠቡ ነው:: ሁለተኛ
ደግሞ መሊሳን ለመሰ ኢትዮጵያ ተራማጆች የሚያደርገው ጥሪ በመካከላችን በሰላም መሰስተኛ
ልዩነቶች እንደሁኔታው አስፈኒነት በይፋ ወይም በህቡዕ ሃቀኛ ውይይቶችን እንድንገደምርና የተ
ገለ አንድነታችንን በተወሰኑ ተጨባጭ የትግል መስኮች ላይ እንደገና መገንባት እንድንገደምር
ነው::

1. ከሁሉ መጀመሪያ መሊሳን የሚያቀርበው ጥሪ ለፀረ ሕዝቦች መሣሪያነት ይብቃ!
የሚል ጥሪ ነው:: ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች ይኸንን ያህል በገፍ ቢታሠሩ፣ ቢሰቃዩና ቢረ
ሸኑ ለዚህ ሁኔታ ተጠያቂው ደርግ ብቻውን እንዳይደለ ገለጽ ነው:: የአድርባይ ድርጅቶች
መሪዎች የኢትዮጵያን አብዮት ለፍርፋሪ በመሸጥ፣ ከአብሮቻቸው አንዳንዶቹ ደግሞ በዚህ በተ
ወጣደቻን ለመሳት እያባለሉ በጥቅም:: ይህ እነዚህን ኃይሎች በታሪክ ፊት ቢያስጠይቃቸው
የሚኖር አብዮት ተግባር ከጨቀላነት፣ ከጥፋን ግላጅ ከስገብገብ አድርባይነት ሌላ ምንም
ምክንያት የለውም:: መሊሳን አባላት "ማርክሲስት ሌኒኒስት አይደለንም" ቢባሉ አንጋገ
ቢያገቡ ቢያገቡ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መድረክ ላይ የቀሙ ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔ
ሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይሎች ናቸው:: ስለሆነም የአድርባይ ድርጅቶች
መሪዎች ከመሊሳን ጋር ያለው ልዩነት በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ በአብዮት ሠፈር ያለ ልዩነት
መሆኑን አያውቁ ይህ ቀራኒ በውይይት ሳይሆን በአሥራትና በርሸና እንዲፈታ መወተወታቸው
ምን ያህል እንደታወሩና ምን ያህል ለፀረ አብዮት አገልጋዮች የሚያሳይ ተግባር ነው::
ወጤቱም የአብዮትን በሬር አያደከመ የፀረ አብዮትን ሠፈር የሚያጠናክር መሆኑ በነዚህ
ድርጅቶች በራሳቸው ውስጥ ለሚገኙ ሃቀኛ ታጋዮችም መቃብር መቆፈር እንደሆነ ዛሬ በአቋም
ራጥር ማስረጃ ነው:: አንዳንዱ ተራማጅ አውቆም ሆነ ሳያውቅ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት
ፕሮግራም ጠላት አድርጎ ካሰወነባቸው ኃይሎች አንዱ ገለሰብ እንዲሁን ለፀረ ሕዝቦች ቢጠቀ
ምና አባልና ሲሆን ለኢትዮጵያ ተራማጆች ሠፈር መዳከም አስፋሪ አስተዋጽኦ ማድረጉ፣ ሕብረ
ታቸው እንዳይመሠረት ጠባቂ የሆኑና የጦርነት ገበያ ለመገንባት ማገዙና ዘር ዘር ደግሞ
ፀረ ሕዝቦችን ለማጠናከር የራሱን መቃብር መቆፈሩ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርበታል:: በተ
ከመተባበር ሆነ በሉ ቢቀጠብ የአብዮት በሬር እንዳይዳከም የሚፈለገውን አስተዋጽኦ ከማይ
ረገ በላይ በፀረ ሕዝቦች ሴራ በመፍረክረክ ላይ ያለው የተራማጆች አንድነት መሰብ እንዲ
ቆም በጣት እንዲያብር ጫድረግ ስለሆነ አንዱን ጊዜ ወይም ጊዜት ከማጓን አዱግ አለም
ዉ ወደር የሌለው አስተዋጽኦ አደረገ ማለት ነው::

ከዚህ የተነሳ ነው ዛሬ መሊሳን ለተራማጆች ህብረት መሠረት ለመጣል ይህ የመተማመን
ተባበር፣ የመንፈሳዊ መሰረት በመካከላችን እንዲሰፍን ከሁሉ አስቀድሞ ይህ የጥቃ
የመጣቀን መርህ ከመካከላችን ወርሶ መነቀል አለበት የሚለው:: ለዚህ ነው ለፀረ ሕዝቦች
መሣሪያነት ይብቃ! ብሎ የሚያስተጋባው::

ከዚህ ጋር የተያያዘ ሌላው የመሊ ኢትዮጵያ ተራማጆች ተግባር መሆን ያለበት ጉዳይ አለ::
ዛሬ በደርግ እሥር ቤቶች በመሰቃየት ላይ የሚገኙት በሺህ የሚቆጠሩት የመሊሳን አባላትም
ሆኑ የሌሎች ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች አባላት፣ እንደዚሁም በፍር ቁጥር የሌላቸው
ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች በሙሉ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መድረክ ላይ የቆሙ
የአብዮት ኃይሎች በመሆኑ በአስቸኳይ እንዲፈቱና አብዮታዊ ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ ተራማ
ጆች ሁሉ ትግላቸውን ማስተባበር አለባቸው::

2. በልዩነቶቻችን ላይ እንወያይ!

ይህ ጥሪ "እንደአጣዳፊ ተግባር" ብሎ መቀረጹ ራሱ እስካሁን ያሉት በኢትዮጵያ ተራማ
ጆች መካከል የነበሩት የነሳን ያለመተማመን መርህ ምን ያህል ፍሬ እንደበጠ የሚያሳይ
የኢትዮጵያ ተራማጆች ጠቀሜታም የሚያስከትል ማሣሪያ ነው:: በተራማጆች ሠፈር በተለይ ከሁ
ለት ዓመት ወዲህ ፀረ ሕዝቦች ሆነ ብለው ያስፋፉት ይህ መርህ በልዩነቶች ላይ እንዳን
በጥሩና በርጋታ ከመነጋገር ያለበትን ውይይት እፍኖች ይገኛሉ:: ፀረ ሕዝቦች ከውይይት መገባ
ባት፣ ከመገባባት አንድነት፣ ከአንድነት ደግሞ ድል እንደሚገኝ ያውቃሉ:: ስለዚህ ይህ

ውይይት እንዳይካሄድ ባገኙት ተንኮል ሁሉ ይጠቀማሉ:: ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አፍነው
መያዛቸው አንዱ ምክንያት በዲሞክራሲያዊ ውይይት ከሚደርስባቸው መጋለጥና በተራማጆች ሰፈ
ር በሃቀኛ መሠረት ላይ የተመረኮዘ አንድነት እንዳይኖር ለማድረግ እንደሆነ ግልፅ ነው::
አብዮታውያን ግን "ዲሞክራሲ ያለምንም ይደረጋል ውይይት አይቻልም" ብለው ዝም አይሉ
ም:: በልዩነቶች ላይ መርያየት ለአብዮት ሂደት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ በመረዳት ይ
ህ ውይይት እንዲኖር ያለማቋረጥ መታገል አለባቸው::

ነገር ግን ይኸንን ውይይት የሚፈሩ የሚፈሩ የሰየሳቸው ፀረ ህዝቦች ብቻ አይደሉም:: የ
አድርባይ ድርጅቶች መሪዎች በዚህም በኩል አብሯቸው የሆነ ተልእኮአቸውን በያካሂዱ ቆይተዋ
ል:: ካለፈው ስህተታቸው ምንም ትምህርት ያልቀሰሙ እንደነገሩ የ"ግራ" አድርባዮ አሀአ
ፓ ቀሪዎች ዐጣቶ ርሃቀኛ አብዮታዊ መሥመር ላይ እንዳይሰለፍ ውይይትን ለማፈን ቀደም በ
መበራይ የተሰለፉት፣ ያህል ዛሬ ደግሞ በተለይ በዐጣቶ ጨቃስነት በመጠቀም፣ የቆየ ጥላቻ
ና መጠራጠር እንዲጠሩ ለማድረግ እየሞከሩ ናቸው:: ቀደም ብሎም ቢሆን የኢሀአፓ መሪዎ
ች ሃቀኛው ተከታዮቻቸው ነገሬ ገብተው ዐይአብዮቱ በሬር እንዳይደበለቁባቸው ሲሉ ውይይት
ን ለማፈን "አታነጋግሩ አትመራመሩ" ብቻ ሳይሆን "ከፊውዶች ጋር አንድ ላይ አንነጋገር አይ
ቻልም ያዐናበነዱችንጋል" ይሉ እንደነበር እናረጋለን:: ዛሬም ቢሆን የቀኝ ሃይሎች ህብረ
ትና አደህሪ ቅልቅሉያቸ "ከመሊሳን ጋር ያለን ልዩነት በውይይት ሊፈታ የሚችል አይደለም"
ብለው ሲዘጋጥቁ የሚያበዙት ቀደም ኢህአፓ ያበየው የነበረውን የአብዮቱ ... መሥመር ተራማ
ብቻ ብቻሆን ዲሞክራሲን አፍነው በደረቁና አብልቶ ቅስቀሳቸው ህዝቡን አደናቀረው በጠ
መንጃ አፈሙዝ ለዘላለም ለመግዛት ያሰቡትን ዐኖትም ነው:: ይህ ፓሊቲካቸው በኢትዮጵ
ያ ተራማጆች ... ሰላም ልዩነቶች ከ"ግራ" አድርባዮች ጋር የተደረገውን ያህል አ
ነቧን ምንም አይነት የረባ ውይይት እንዳይካሄድ አድርጓል:: በዚህም የተነሣ የአብዮቱ
በሬር አባል የሆኑት ሃይሎች ተራ በተራ እንዲመቱና እንዲዳከሙ ተደርጓል::

ከዚህ አባዛኝ ሁኔታ ለመውጣት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በተሰለ
ፉ ሃይሎች መካከል ከመቸ በይፋ፣ ካላመቸ ደግሞ በህቡዕ ውይይት ያስፈልጋል ስገል የው
ይይት ነጥቦች ምን ምን መሆን አለባቸው?

የመጀመሪያው የውይይት ነጥብ ዛሬ ለፀረ ህዝቦች አመፅ ተጋልጠው በየእሥር ቤቱ
የሚማቀቁት የመኢሶን፣ የኢጭአት፣ የዐዝአደር ሊግ፣ የአብዮታዊ ሰደድ፣ የማሌሪድ አባላ
ት፣ ሌሎች ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች፣ እንዲሁም በኢህአፓ ውስጥ አብዮታዊ መስመር ይ
ከተሉ የነበሩ የጀብደኛ አመራራቸውን ጭፍቅነትና የቀልበሽ መሥመራቸውን ከሓዲነት በርገፕ
የተረዱ ተፃናበደው የነበሩ ሃቀኞች ጭምር — እንደአብዮቱ ጠላቶች የሚቆጠሩ ሃይሎች ናቸው
ወይስ አይደሉም የሚለው ጥያቄ ነው:: መኢሶን እንዘዘህ ጓዶች የአብዮት ጠላት አይደሉም
እንዲያውም ዛሬ በፀረ ህዝብ ሃይሎች እጅ ገፍና መከራ በመቀበል ላይ ያሉት በሃቀ ለብ
ሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትየሰሙና ሊቆሙ የሚችሉ ዐገኞች በመሆናቸው ነው ይላል::

እነዚን የሌላ ድርጅት አባላትን፣ እነዚን ያልተደራጁ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ግለሰቦችን
ቀርቶ በአንድ ድርጅታዊ መዋቅር ትብብረው አብረዋቸው የተዋደቁትን ጓደቻቸውን የከዱና ለ
ጠላት አጋልጠው የሰጡ አንዳንድ አድርባይ "መሪዎች" በርግጥ ለዚህ መልባቸው ይሽ ሁሉ
በሺህ የሚቆጠር ታጋይ አብዮትን ከድተል፣ ታጋይ የኢትዮጵያ ልጆች እና አተለሥቶ ብቻ ነን፣
እንደሚሆን ገልፅ ነው፡፡ ከዚህም "አስተባበበ" ተነስተው በጠቅላላ በኢትዮጵያ ተራ
ማጆች ላይ ለድርጅቶቻቸውም ውስጥ ባሉ ሃቀኞች ጭምር / አሠራቶ፣ ጭፍጨፋው፣ ርሸናው አ
ንዲቀጥል እንደሚገፋፉ የታርቀ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ እርስ በእርስም ይወያዩ፣ ራሱን
ይጠይቅ፣ ከሌሎች አብዮታውያንም ጋር ሃሳብ ይለዋወጥ የምንለው በድርጅቶች ውስጥ ያለውን
ሃቀኛ አብዮታዊና ገና ያልተደራጀውን ማርክሲስት፣ ዴሞክራትና አገር ወዳድን ነው፡፡ ከማ
ንኛውም የነውን ከበርቴ አልሁ፣ ከማንኛውም የጉዱን ስሜት በራቀ መንፈስ፣ ከሁሉም በላይ
ለኢትዮጵያ አብዮትና ለበዝሬዊ ነፃነቷ በሚቆረቆር መንፈስ የሚካሄድ ውይይት መአበን ከሁ
ለት ዓመት ጀምር የሚጠቀመውን ዛሬ በተጨባጭ በሃገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ላይ የተመበከረ
ውን ሃቅ እንገልተ ያበያል፡፡ ይህ ሃቅ ሌላ ምንም ነገር ባይሆን በበዝሬዊ ዴሞክራሲያዊ
አብዮት መድረክ ላይ ቆመው በሚታገሉ ሃይሎች መሀከል ያሉት ልዩነቶች በሁለተኛ ደረጃ የ
ሚታዩ ልዩነቶች ናቸው የሚለው ሃቅ ነው፡፡ ከዚች መሠረታዊ ሃቅ ላይ መድረስ ቢቻል ለመ
ላ ኢትዮጵያ ተራማጆች አንድ ትልቅ የትግል አንድነት መድረክ ተከፈተ ለማለት ይቻላል፡፡
ልዩነቶች በውይይት እንዲፈቱ፣ መጠቀም፣ ማበደድ፣ ማሠር፣ መረሸን እንዲቆም የኢትዮጵያ
ተራማጆች በሙሉ በአንድነት የሚታገሉበትን የአብዮት ባለቤት የሆነውን ሰፊ ህዝብ በአንድ
ዕንቋ የሚቀበቅሉበትና የሚታገሉበት የጋራ መድረክ አገኙ ማለት ነው፡፡ ለአዲሱ የቀኝ
ሃይሎች ህብረትና ለጠቅላላው የፀረ አብዮት ሃይሎች "የከረፍለህ ገዛ" ቢራ አንድ ማርክ
ሽ ተገኘ ማለት ነው፡፡

ሌላ የውይይት ነጥብ ዛሬም እንደዛሬ ዓመት የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ለኢትዮጵ
ያ አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ እዚህም ላይ የመሸበገና
የተቀረተ ሃቀኛ አብዮታውያን መልስ ገልፀ ነው፡፡ እንዲያውም ባለፉት ሁለት ዓመታት በአ
ብዮታችን ላይ ለደረበው ውድቀት ሁሉ ለህዝባዊ ድርጅቶች መፈረረስም ሆነ ለቢሮክራሲው
መንገስ፣ ለተራማጆች ህብረትም መንኰታኰት መውጣትም ሆነ ለአያንዳንዱ አብዮታዊ ድርጅት
መዳከም፣ ለበዝረበሮች የአክራሪነት መበትም መረገጥ ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ
አንድነት ከፍተኛ አደጋ ላይ መውደቅ፣ የአብዮታችን አደል በርጭ ሃይሎች ቀጥር ስር መውደቅም
ሆነ የኢትዮጵያ በዝሬዊ ነፃነት መደፈር፣ ለዚህ ሁሉ እንዲ ምክንያት ይህ አንገብጋቢ ጥያቄ በወቅ
ቱ ተገቢ መልሱን አለማግኘቱ ነው እንላለን፡፡ በየድርጅቶቹ ቀገጠ ላይ ፈጥ ብሎ በነበረ

አድርባዮች የተነሳ ተወናበደ "ከቂ ዴሞክራሲ አለ" ሲለ የነበረው ሃቀኛ ዛሬስ በሃገራችን
የነገሠውን ፀረ ዴሞክራሲ ሲመለከተ፣ በየድርጅቱ ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ባለው ሃቀኛ ዴሞ
ክራትና አገር ወዳድ ላይ የሚደርሰው ገና በራሱ ላይ ሲሰማው ከተጨባጭ ሁኔታ የቀሰመው
ትምህርት ምንድን ነው? እጅ ለእጅ ተያይዞ ለዴሞክራሲያዊ መብቶች መታገል፣ ለዚህም ዓላማ
የአብዮቱ ባለቤት የሆነውን ሰፊ ሕዝብ በይፋም ሆነ በህቡዕ ማታገል ያስፈልጋል ወይስ
አያስፈልገውም? ይሕም አንድ ሌላና ከፍተኛ የውይይት ነጥብ ነው፡፡

ሶስተኛ ሌላ የኢትዮጵያ ተራማጆች ሊወያዩበት የሚገባው ነጥብ ብሄራዊ ነፃነታችንንና
የሃገራችንን ክብር የሚመለከት ነጥብ ነው፡፡ ከሰፊው ሕዝብ እየራቀና እሱን እየተቃረነ
የተጠናከረው የቀኝ ኃይሎች ህብረት በሰፊው ሕዝብ ላይ መተማመን በመፍራቱ፣ እምነቱን በውጭ
ኃይሎች ላይ መጣሉና በቀኝ ኃይሎች ህብረት ገብዥ በሺህ የሚቆጠሩ የባዕድ ወታደሮች ሃገራ
ችን መምጣቱ መሠረታዊ አብዮታችንን አራምደታል ወይስ ወደኋላ ጎትቶታል? ለኢትዮጵያችን
በአፍሪካም ሆነ በሌሎች የዓለም ሕዝቦች ፊት የነበራትን ዝናና ስም ጠብቆታል ወይስ ስሟ
ገና ታሪኳን አጉድፎባታል? ራሷን የቻለች ኩሩ አገር አድርጓታል ወይስ የባዕድ ኃይሎች
ተቀጣሪ ሆናለች? መሲበገና ሌሎች የኢትዮጵያ አብዮታዊያንና አገር ወዳዶች የቀኝ ኃይሎች
ህብረት በውጭ ኃይሎች ተማምኖና በነሱ ዱጋፍ ተጠናክሮ አብዮታችንን አሁን የሚገኝበት አስ
ቸጋሪ ሁኔታ ላይ ጥሎታል፣ የውድ እናት አገራችንንም ክብር አዋርዶታል ይላሉ፡፡ በአድርባይ
የድርጅት መሪዎች አሉባልታ ተወናብደና በጊዜው በኢትዮጵያ አብዮትና በሃገራችን ህልውና ላይ
አፍጥጠው በነበረት ከባድ ፈተናዎች ተማርክ የመሲበገን "ራስን በራስ መቻል" "እርዳታ
ን በሁለተኛ ደረጃ መመልከት" "ለብሄራዊ ነፃነት ቀናተኛ መሆን" "ዐምነተን በ28
ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ መጣል" የሚሉ መፈክሮች መረዳት አቅቶት የነበረው ሃቀኛ
ታጋይ ዛሬ በሃገራችን ከሚያየውና ከሚሰማው ሁሉ ምን ተጨባጭ ትምህርት አገኘቷል? ዛሬ
ካለንበት ማጥ ውስጥ ለመውጣት በነዚህ መፈክሮች ስር ተሰልፎ ለአብዮታችንና ለእናት አገራ
ችን ክብር የኢትዮጵያ ተራማጆችና አገር ወዳዶች ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን ማገናውም የውጭ
ተጽእኖ መቋቋም አለብን፡፡ ሰፊውንና በአገር ፍቅር ስሜት ዓለም ያደነቀውን የኢትዮጵያ
ሕዝብ ትግሉን እንዲያፋፍም መቀስቀስ አለብን ወይስ የለብንም? ይሕም ሌላ የውይይት ነጥብ
ነው፡፡

አራተኛው የውይይት ነጥብ ሃቀኛውን የተራማጆች ህብረት የሚመለከት ነጥብ ነው፡፡ ለሃ
ቀና የተራማጆች ህብረት ዋናው እንቅፋት የአድሃሪዎችና የየስርጎገቦቻቸው የመከፋፈል ሴራ፣
የአብዮታዊ ስደደም ሆነ የሌሎች አድርባይ ድርጅቶች መሪዎች የበለጠን ጥም መሆኑ እየታወቀ
ይህ ችግር በመሲበገ "አበጠ ራሱ ወደፓርቲ ለመለወጥ ፍላጎት" ሲለጠፍ ቆይቶ ነበር፡፡
ዛሬ ይሕ ሁሉ በደልና ገፍ ደርሶበት አሁንም ለሃቀኛ ተራማጆች የሕብረት ጥሪ የሚያደርገው
ማን ነው? ሲያሸቸው ድርጅቶችን እንዳለ በ "አዋጅ" ከተራማጆች ህብረት የሚሰርዙት፣ ሲያ
ሻቸው በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ገብተው "ሹመር" የሚያካሄዱት፣ ዘር ዘር ደገው አበጠውና
ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ተዋህደው ራሳቸውን ወደ "ወዝአደር ፓርቲነት" ለመለወጥ ዳርዳር የሚ
ሉት የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ሃቀኛ ህብረት እንቅፋት እነማን ናቸው? የአብዮታዊ ሰደድ
መሪዎች ወይስ መሲበገ? መሲበገ አሁንም ራሱን ብቻውን ወደፓርቲ የመለወጥ ሃሳብ የለውም፣
አሁንም ሃቀኛ ከሆኑ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ጋር ለመወያየት የአብዮቱን ሰፊር ከመጠናት
ይልቅ ለመሰበሰብ ይታገላል፡፡ የኢትዮጵያን አብዮታዊያን አንድነት የሚሻው ሃቀኛ ታጋይ
ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ካየውና ከቀሰመው ተጨባጭ ትምህርት ተነስቶ የሚደርሰው የትግል
አቅጣጫ ምንድን ነው? እንደዛና ለጠንካራና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ እንደዛና ለሃቀኛ ዴሞ
ክራሲያዊ ውይይት ይታገላል ወይስ አይታገልም? ከአድሃሪው ቢሮክራሲና ገወሰ ከበርቴው ተመ
ራርተው በኢትዮጵያ ሕዝብ ትከሻ ላይ ፀረ ወዝአደር የሆነ የዚያድ ባሬው ዓይነት "የወዝ
አደር ፓርቲ" ሲጭኑ ዝም ብሎ ይመለከታል ወይስ ከሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ጋር ትብ
ብሮ በወዝአደሩ፣ በአርሶአደሩ፣ በመለዮ ለባሹና በአብዮታዊው ምሁር እጅባቢ ባሉቸው መንገድ
ሁሉ የሃቀኛውን የወዝአደር ፓርቲ መሠረት ለመጣል በትጋትና በቆራጥነት፣ በዲሲፕሊንና በተ
ዐገሥት ይሠራል? ይሕም አንድ የውይይት ነጥብ ነው፡፡

በዚህ መልክ ብዙ የውይይት ነጥቦች እንደመገደርደሪያ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ዋናው
ነጥብ አሁን እነዚህን ዘርዝሮ መጨረሱ ላይ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ የኢትዮጵያ ተራማጆች
ካለፉት ስህተቶቻቸው አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመው ከጠባብነት በጸታ ተላቀው ለፀረ ሕዝቦች
መሣሪያነታቸውን ዛሬውኑ ማቆማቸውና በልዩነቶቻቸው ላይ በግልፅ ለመወያየት መወሰናቸው ነው፡፡
ይህ አርምጃ ከተወሰደ ከነዚህ የመገደርደሪያ ነጥቦች ሌሎች ለኢትዮጵያ አብዮት መሠረታዊ
የሆኑ ጥያቄዎች ይኖራሉ፡፡ በየጊዜው ደግሞ ከተለዋዋጩ ሁኔታ ጋር አብረው የሚፈለቁ የመወ
ያያ ነጥቦች ይኖራሉ፡፡

ውይይቱ እንዴት ይካሄድ? ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ይህ ውይይትና የሚያስከትለው መግባባት
እንዳይደርር ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አፍነው ይዘዋል፡፡ በአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ
ለየት ያለ አቋም ያለውን ሁሉ "ቀኝ መንገደኛ" "የቀኝ ክንፍ" "የመሲበገ ሰርጎገብ"
እያሉ ያሠራሉ፣ ይረሽናሉ፡፡ ከዚህም በረቀቀ ዘዴ በተራማጆች መሀከል ሊፈጠር የሚገባው መተ
ማመን እንዳይኖር፣ ጥላቻ፣ ጥርጣሬና መከፋፈል እንዲነገሥ ሌት ተቀን ይሠራሉ፡፡ እዚህናው
ወጥመዳቸው ውስጥ ካልወደቅን የዴሞክራሲያዊ መብቶች መታፈን የተራማጆችን መወያየትና

መቀራረብ ያጊትት እንደሆነ እንጂ ወርሰው አያፍኑም፡፡ ስለሆነም የሚተማመኑና የሚተቃወቁ ተራማጆች ዛሬ ነገ ባሉሉ ከላይ በጠቀስናቸውና በሌሎች አንገብጋቢ በሰው በሚቀጥፈቸው አርእስቶች ላይ በሀሶና በደሊገሊን የሚካሄድ ውይይት ይጀምራ እንላለን፡፡ በገበሬ ማህበራት፣ በዐዝእደሬ አካባቢ፣ በቀበሌዎች፣ በወጣቶች፣ በቢቶች፣ በመሰቀ ሰባኩ ውስጥ፣ በዩሁራን፣ በአገር ወዳዶችና ዲሞክራት የጦርና የፖሊስ መኮንኖች አካባቢ በሃቀኛነታቸው፣ በቆነገሮናትታቸው፣ በመስጠረኛነታቸው፣ በሃገር ፍቅራቸው የሚተዋወቁ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያሉበት አካባቢ እነዚህን የአብዮታችንንና የሃገራችንን እድል የሚወስኑ ጥያቄዎች አያነሱ በጥንቃቄ መወያየት ይጀምራ፡፡ የመኢሶን አባላት በሙሉ ለዚህ ውይይት ዝግጁ ናቸው፡፡

ከዚህ ከሃቀኞችና በሚተማመኑ ኢትዮጵያውያን መሀከል ከሚካሄድየመጀመሪያ ደረጃ ውይይት አልፈን ስመሄድ መዘጋጀት አለብን፡፡ ይኸውም ድርጅት ለድርጅት መካሄድ ያለበት ውይይት ነው፡፡ እርግጥ ከላይ እንዳልነው ዛሬ ቀደም ቢል የነበረት ተራማጅ ድርጅቶች አመራሮቻቸው በተከተሉት የከረ ፖለቲካ የተነሳ በመበታተን ላይ ናቸው፡፡ የከፋውም ከዩቿል፡፡ ከሃቀኛው ብዙ አንዳታፈስ በየእስር ቤት ነው፡፡ ቢሆንም ምንም እንኳን አመራሮቻቸው ቢከዱ ቅሉ የእነዚህ ድርጅቶች ሃቀኛ አባላት በቅደሚያ አሰፈለገውን ውይይት በዐሰጣቸው ካካሄደው ሃይላትን በሰበሰቡና አደርጅተው በአድሃሪው ቢርከራቢ የተገነባቸውን አመራር ወዲያ ትተው ገሃቀኛ አብዮታውያን ጋር ከግለሰብ ውይይት አልፎ በ[illegible] ደረጃ ውይይት ለከፍት [illegible]ችላሉ፡፡ በዚህ ውስጣዊ ውይይት የሚደርሱበቸውን ሊያቀርቧቸውና ውይይት ሊጋበዙበቸ ይችላሉ፡፡ በዚህም ደረጃ ቢሆን መኢሶን ከተራማጆች አካባቢ በሚቀርቡ ትንተናዎች [illegible]ይ ተመርኩዞ ሃሳቡን ይገልጻል፡፡ ይህ በየድርጅቱ ውስጥ የቀረት ሃቀኞች በውስጣቸው የሚያካሂዱት ውይይት ከሌሎች ተራማጆች ጋር ከላ[illegible] በመቀስነው [illegible] ደረጃ ከ[illegible] ውይይት ጋር አይፃረርም፡፡ እንዲያው ተጋግዞና አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ናቸው፡

በሌላ ደረጃ ደግሞ በውጭ አገር ያሉ የተራማጅ ድርጅቶች አካሎች የሃቀን ብሄረሰብ እንቅስቃሴዎች አካላት፣ የተበታተኑ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች እንዲሁም የ"ገሬ"ና የቀኝ ለድርበይ ድርጅቶች ደጋፊዎች የነበሩና ሃኖና ወገኖች፣ በተግባራቸው ንቁና አማከይነም ሆነ ድርጅቶቻቸው በሚከፍቱላቸው መድረክ ሁሉ ሊያካሂዱት የሚችሉት ጠቃሚ [illegible] አለ፡፡ እርግጥ አሁኑ የቀኝ ሃይሎች ህብረት በተለ[illegible] የኢትዮጵያን ዐሬቶች የትግል [illegible] በአፈሙዝ ሃይል ያንበረከከ ከመሰለው በኋላ በ[illegible] ያለውንም ወጪትና አብዮታዊ ሃይል ሁሉ በልዩ ልዩ ተፅዕና ለመበታተንና ለጫከም እየተሯሯጠ መሆኑን ለናውቃለን፡፡ ይሁንና በልዩ ልዩ ድርጅቶች ደጋፊዎችም ሆነ በጠቅላላው ለኢትዮጵያ አብዮት፣ በ[illegible] ነፃነት በ[illegible] ሃይሎች መሃከል ውይይት ለሚካሄድ በአገር ውስጥ [illegible] በመታገል ላይ ካለው ሃይል በውጭ አገር የሚገኙት የኢትዮጵያ ተራማጆች የተገለ እደል አለቸው፡፡ ይኸ የተለየ ሁኔታቸው በበለቸው እደሌ ተጠቅመው ከሚ[illegible]ውም

ቡድን ስሜት በላይ ለዚች እናት አገራችን ክብርና ነፃነት በ[illegible] ቆርቆር ቆንፈስ ተነባስተው፣ የተማሪ ማህበሮቻቸውም ሆኑ ድርጅቶቻቸው በሚከፍቱላቸው መድረክ አማካይነት ነፃና ዲሞክራሲያዊ ውይይት አያካሂዱ፣ ለተራማጆች የትግል አንድነት ምባሊነት ያለው አስተዋፅዖ ሊያደርጉ ይችላሉ ብለን እንገምታለን፡፡ በዚያም ያሉ የመኢሶን አባላትና ድርጅታዊ አካሎች ለእንዲህ አይነቱ አብዮታዊ ተልእኮ ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ ናቸውም፡፡

ውድ ጓዶችና ጓዲቶች፣ ዐገኖችና እህቶች!

ለኢትዮጵያ ተራማጆች ህብረት ጥሪ ሲደረግ ከዚህ "ለጠባት መሠሪያነት ይብቃ" "ተራማጆች.እንዐያይ" ከሚል ጥሪ አልፈን ለመሄድ ብንችል ኖር ምንኛ ደስ ባለን ነበር! ነገር ግን ዛሬ ቀደም ቢል የነበረት ተራማጅ ድርጅቶች ሁሉ ያሉበት የመፈራረስ ደረጃ፣ በተራማጆች መሀከል አድሃሪዎች የነዙት የጥርጣሬና የአለመተማመን ሁኔታ ቢታይ ዛሬ ጥሪያችን ከነዚህ "የመጀመሪያ ደረጃ" ጥሪዎች አልፍ ሊሄድ ይችላል ወይ?? ዛሬ ባለንበት ሁኔታ በነዚህ ሁለት ዝቅተኛ ነጥቦች ላይ አስቀድመን ባንስማማ፣ እነዚህን በሃቅ ከሥራ ላይ ለማዋል ባንታገል፣ "ተራማጆች እንዲህ እንሥራ፣ እንዲያ እናድርግ" እያልን ከፍተኛ መተማመንን ድርጅታዊ ቅንብርን የሚጠይቁ የጋር ተግባሮችን እንዘርዝር ብንል ሁዱ ቢያውቅ ደር ማታ አይሆንም ወይ?? ፊስን ማታለል አይሆንም ዐይ?? እና ይሆናል እንላለን፡፡ ስለዚህ ነው ይህ "እንደገና ለተራማጆች አንድነት ጥሪ" ብለን የበነዘርነው ጥሪያችን ከነዚህ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች አልፍ ሌላ "ተግባር" ውስጥ ዘርዝር መግባት ያልታየን፡፡ አሁን ካለንበት ደረጃ ተነስተን እስቲ ለጠባት መሠሪያነት ይቁም፣ እስቲ በአብዮት ጥያቄዎች ላይ ሁኔታው እንደሚፈቅደው በየደረጃው ዐይይት ይጀመር! ይኸ ከሆነ በኋላ መኢሶን አስፈላጊ ሆኖ ቢያገኘው ከዚህ አልፍ የሚሄድ ሌላ መርሀ ግብር፣ ሌላ የድርጊት ፕሮግራም ያቀርባል፡፡ እንደሁኔታው፣ እንደተራማጆች አንድነት ሥር መሰደድ ታይቶ ይህ የጋራ መርሃ ግብር ወይም የድርጊት ፕሮግራም በእርግጥ መኢሶን ብቻ ባይሆን የኢትዮጵያ ተራማጆች ተወያይተው የሚስነዝረት መርሃ ግብር ሊሆን የሚይችልበት ወ[illegible] መከንያት የለም!

ለማጠቃለል፣ ከላይ በሰፊው እንዳብራራነው ዛሬ በአገራችን ምንም ያህል ገፍና ጭፍጨፋ በተራማጆች ላይ ቢወርድም ቅሉ ተጠባጩ ሁኔታ የአብዮታውያንን እጅ ትከበለኝነት ከአለት እለት እያጎላ እያባየ፣ የቀኝ ሃይሎች ህብረት ከሥራና ከህይወት ደግሞ እንደዚሁ እያጋለጠ የሚሄድ አመቺ የፖለቲካ ሁኔታ አለ፡፡ በዚህ አገባር አሁኑ የቀኝ ሃይሎች ህብረትና የበላይ አዛዦች የኢትዮጵያ አብዮትም ሆነ በሃገሪቱ ክብር ለሚያቀርቡቸው እንገብጋቢ ጥያቄዎች ለእንዳቸውም ተገቢ መልስ ሊሰጡ ስለማይችሉ ከኪሣራ ኪሣራ፣ ከመጋለጥ መጋለጥ እንጂ ካሁኑ የተሻለ እድል እንደማይገጥማቸው ባይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ልክ ደግሞ ማንኛውም መስዋዕትነት እየከፈሉ በሃቅ ለአብዮትና ለእናት አገር ክብር ለ[illegible] ሃይሎች ጊዜው ይበልጥ እያመቸ ይሄዳል፡፡

በሀገም ኪሣራቸውን ለመሸፈን የተራማጅን ሰፈር ለማድከም ፀረ ሕዝቦች በአብዮታዊያን
ላይ ያወረዱት በታሪካችን ምንም ዓይነት ተወዳዳሪ የሌለው ግፍ የተነሳ ከዚህ በፖለቲካው
አገሪር አዉን አመቺነት ጋር የሚነጻጸር ድርጅታዊ ጥንካሬም ሆነ የተራማጆች አንድነት አለ
ለማለት አይቻልም:: ግን ይህ ዘላቂነት የለውም:: በተለያዩ አድርባይ አመራሮች ከሥረት
የተነሳ አርነት ዛሬ በዙ ሃቀኞች ተስፋ በመቁረጥ፣ በመበታተን፣ ተደራጅተው መታገልን
እርም ብለው በመተው ላይ ይገኛሉ:: ባይወዱት ባይነሳ፣ ተስፋ መቁረጥና አገደገና ማገለ
ሬሬት ባይ ..ረቋጠት የመዉረጃውን ገቡን የመታ አበዩት በየትም አገር ታሪክ ታይቶ አይታ
ወቅም:: ይህ ሁኔታ ለና ለጊብ በመበለገም በብዙ አበዮቶች ታሪክ ተደጋግሞ የታየ ሁኔታ
ነዉ:: በለሆነም ዛሬ አድርባይ መሪዎቻቸው በተከተሉት የከሀ: ፖለቲካ መሥመር የተነሳ
ሕዝቡ የተፋቸው፣ ግን ደገሞ በሃቀኛነታቸው የተነሳ በአድሃሪው በርከራሲ ሙሉ ቁጥጥር ሥር
የወደቀው የቀን ኃይሎች ሀበረት የሚያስቡዳቸው በፍር ቁጥር የሌላቸው ገራ የተጋቡ ጓደኞ
ቸን አሉ:: እነዚህ ወገኖቻችን አንድ ነገር ማወቅ ይኖርባቸዋል:: ሰፍር፣ ተሸጠው በሬ
ውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የከዱት አድርባይ መሪዎቻቸው ለተከተሉት ፖለቲካ ዘለዓለማቸውን ቢስ
ቀቆ መኖር የለባቸውም:: በሃቀ ለበሬው ሕዝብ የቆሙ ከሆኑ ለኢትዮጵያ አብዮትና በሂራዊ
ከበር የሚደረገው ትግል ገና ከፊታችን ነው:: ያለፈውን ሁኔታ በጥሞና መርምረው፣ ከተፈጸሙ
ስህተቶች አስፈላጊውን ትምህርት የከመው ወደፊት ለመራመድ ከተነሱ አሁን የተያዘውን
ተስፋ መቁረጥና መበታተን ተወጥተው ለመጥው ትግል የሚፈለገባቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ
ይቸላሉ:: ማድረገም አለባቸው:: በዚህ ጥረታቸውም የመላ ኢትዮጵያ በሸሊስት ገቀናቂ
ምገዝም አንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ነገም ከጉኖቸው ተሰለፍ ለኢትዮጵያ ተራማጆች የትገል
አንድነት፣ ለአብዮታችን ድልና ለእናት አገራችን ክብር እየተካሄደ ወደፊት ለመራመድ ዝግጁ
መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል::

ተስፋ መቁረጥና መበታተን ይብቃ!
የኢትዮጵያ ተራማጆች ሁሉ በአንድነት ወደፊት አንገፋ!
የነፃ፣ የተደራጀ፣ የታጠቀ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል!